Addis Ababa University Libraries


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምናየኮሚዩኒኬሽንኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


# በ2004ዓ.ም. በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት

ተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ

የቀረበ ጥናት


በ

አልታየች ተክሌ


ጥር 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምናየኮሚዩኒኬሽንኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃመርሐ ግብር

# በ2004ዓ.ም. በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያመፅሐፍ ውስጥየሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት

በ

አልታየች ተክሌ

ጥር 2009ዓ.ም.

አዲስአበባ

# በ2004ዓ.ም. በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


ተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ

የቀረበ ጥናት

በ


አልታየች ተክሌ


2009ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ

ስም ጌታቸው አዱኛ (ዶ/ር) ፊርማ ________

ፈታኞች

ስም [illegible] ፊርማ ________

ስም [illegible] ፊርማ ________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለምናፍቀው ቀን ያደረሰኝን እግዚያብሔርን አመሰግናለሁ፡፡በመቀጠል ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ጊዜያቸውን ሰጥተው በየጊዜው ረቂቁን በማንበብ፣ በማረምና የማሻሻያ ሀሳብ በመስጠት ሙያዊ ድጋፋቸው፣ ትዕግስት የተሞላበት ክትትላቸው ሳይለየኝ ለረዱኝ አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አዱኛ ከልብ ሳመሰግን፤ ለማበረታቻቸውና ሁሌም ለሚያደርጉልኝ ትህትና የተላበሰ አቀባበል ልዩ አክብሮት አለኝ፡፡

ከሙያቸውና ከምርምር ጥናት ልምዳቸው በመነሳት ከርዕስ መረጣው ጀምሮ ጠቃሚ ሀሳቦችን በማካፈል ድጋፍ የሰጡኝ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው፣ የቀለም ቆጠራ እርማት ላደረጉልኝ ዶ/ር ታደሰ ሲባሞ፣ በእጃቸው የሚገኘውን መጽሐፍ በማዋስ ያበረታቱኝ የሀዋሣ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን አቶ መላኩ ዋለልኝ፣ አቶ ወንድወሰን በየነ እና በእስታቲክስ ሥራ የተባበሩኝ የሀዋሣ ዩኒቨርስቲ መምህር አቶ ደስያለው ደምሴ ባለውለታዬ ናቸውና ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

እንዲሁም በጥናቱ ወቅት የምፈልጋቸውን መጻሕፍት እንድገለገል ለፈቀዱልኝ ለደቡብ ትምህርት ቢሮ፣ ለሀዋሣ ዩኒቨርስቲና ለሀዋሣ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ቤተ-መጻሕፍት ሠራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለጥናታዊ ጽሑፌ አስፈላጊ የሆነውን ገንዘብ በመሸፈን ላደረገልኝ ትብብር፣ ጥናቱ በትምህርትቤታቸው ውስጥ እንዲካሄድ በመፍቀድና በጥናቱ ዙሪያ የምፈልገውን ትብብር እንዳገኝ ለረዱኝ የየትምህርትቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡

ፈተናዎች ከተዘጋጁ በኂላ አስተያየት በመስጠት ያማከሩኝ፣ ያረሙኝ የክፍለትምህርቱ መምህራን እንዲሁም በሚገኙበት ትምህርትቤት በጊዜው ተገኝተው ፈተናውን በመፈተንና በማረም፣ ለቃለ መጠይቁ የተባበሩኝ መምህራንና በተጠኚነት መልካም ትብብራቸው ያልተለየኝ የተጠኚ ትምህርትቤቱ የ2008 ዓ.ም. የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችና ደከመኝ ሰለቸኝ ሣትል ጥናቱን በኮምፒውተር በመጻፍ ለረዳችኝ ወ/ሪት ትርሲት ኤልያስ ለቀና ትብብሯ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም በትምህርቴ ላይ በቆየሁባቸው ጊዜያት የነበረኝን ኃላፊነት በመካፈል፣ ትምህርቴን እንድከታተል የረዳኝን ባለቤቴን መኮንን ቦጋለ፣ እንደዚሁም በትምህርት ሥራዬ ላይ ያበረታቱኝን ልጆቼን፣ ወንድሞቼን፣ እህቶቼንና ጓደኞቼን ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና....................i
ማውጫ....................ii
የሠንጠረዥ ማውጫ....................iv
አጠቃሎ....................vi
ምዕራፍ አንድ.................... 1
መግቢያ.................... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ.................... 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር.................... 4
1.3 የጥናቱ ዋና አላማ.................... 5
1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ.................... 5
1.5.የጥናቱ ወሰን.................... 5
ምዕራፍ ሁለት.................... 6
ክለሳ ድርሳናት.................... 6
2.1 የተነባቢነት ምንነት.................... 6
2.2 የተነባቢነት ቀመሮች.................... 9
2.2.1 የFlesch (1949) ቀመር.................... 11
2.2.2 የEdward Fry (1977) ግራፍ.................... 13
2.2.3 የGunning'sFog(1952) ቀመር.................... 14
2.2.4 የግንዛቤ ዝግ ሙከራ/CloZe Test/ Wilson Taylor (1953).................... 15
2.3 ለተነባቢነት መኖር አስተዋፅኦ ሚያደርጉ ሀሳቦች.................... 17
2.3.1 ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር.................... 17
2.3.2 ቃላት.................... 19
2.3.3 ዳራዊ እውቀት.................... 20
2.3.4 የፅሑፍ አደረጃጀት.................... 20
2.3.5 የምንባብ ርዝመት.................... 20
2.4 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.................... 21

ምዕራፍ ሦስት........................................................................................ 23
የአጠናን ንድፍና ዘዴ........................................................................................ 23
3.1 የጥናቱ ንድፍ........................................................................................ 23
3.2. የጥናቱ መረጃ ምንጮች........................................................................................ 23
3.3 የናሙና አመራረጥ........................................................................................ 23
3.3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ........................................................................................ 23
3.3.2 የምድቦች ናሙና አመራረጥ........................................................................................ 25
3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ........................................................................................ 25
3.3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ........................................................................................ 26
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች........................................................................................ 26
3.4.1 የሰነድ ምርመራ........................................................................................ 26
3.4.2 ለተማሪዎች የተዘጋጀ የግንዛቤ ዝግ ሙከራ........................................................................................ 27
3.4.3 የፅሑፍ መጠይቅ........................................................................................ 28
3.4.4 ቃለመጠይቅ........................................................................................ 29
3.5.የመረጃ አተናተን ዘዴ........................................................................................ 29
ምዕራፍ አራት........................................................................................ 31
የመረጃ ውጤት ትንተና........................................................................................ 31
4.1. የምንባቦችንተነባቢነት ለመለካትከቀመሮችና ከግንዛቤ ሙከራዎች የተገኙ መረጃዎች........................................................................................ 31
4.1.1የFlesch ቀመር ስሌት........................................................................................ 31
4.1.2 Edward Fry ግራፍ (1977)........................................................................................ 33
4.1.3 ከግንዛቤ ዝግ ሙከራ የተገኘ ውጤት........................................................................................ 35
4.2. ከፅሑፍ መጠይቅ ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች........................................................................................ 40
4.3 በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች........................................................................................ 47
ምዕራፍ አምስት........................................................................................ 51
ማጠቃለያና አስተያየት........................................................................................ 51
5.1 ማጠቃለያ........................................................................................ 51
5.2 አስተያየት........................................................................................ 55
ዋቢ ጽሑፎች........................................................................................ 56

ሙዳዬ ቃሎች....................................................................................................... 59

አባሪ1Edward Fry(1977) graphy

አባሪ 2 የናሙና ምንባቦች ቀለም ብዛት

አባሪ 3 የግንዛቤ ዝግ ሙከራ አንድ

አባሪ 4 የግንዛቤ ዝግ ሙከራ አንድ መልስ

አባሪ 5 የግንዛቤ ዝግ ሙከራ ውጤቶች

አባሪ 6 ለአስረኛክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

አባሪ 7ቃለ መጠይቅ

አባሪ 8_የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነት ለማወቅ ክሮንባኽ አልፋ ውጤት

አባሪ 9 በግንዛቤዝግ ሙከራ አራሚዎች መካከል ስምምነት መኖሩን ማረጋገጫ (ANOVA)

አባሪ 10 ፎቶ ግራፍ

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ ገፅ

ሠንጠረዥ 1 የFlesch(1949) ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥ ........ 13

ሠንጠረዥ 2 የGunning'sFog(1952)ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥ ........ 15

ሠንጠረዥ-3 በናሙናነት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች፣ተማሪዎችና ምድቦች ........ 24

ሠንጠረዥ 4 በFlesch ቀመርየተገኙ የሶስቱ ናሙና ምንባቦች ውጤቶችና ምንባቦቹ የተገመቱለትየክፍል ደረጃ ........ 32

ሠጠረዥ 5 ምንባቦቹ በ Fry ግራፍ የተገመቱለት ክፍል ደረጃ ........ 34

ሠንጠረዥ 6 የሦስቱም ትምህርትቤት የግንዛቤ ሙከራ አንድ የተማሪዎችውጤት ........ 36

ሠንጠረዥ 7 የሦስቱ ትምህርትቤት የግንዛቤ ሙከራ ሁለት የተማሪዎች ውጤት ........ 37

ሠንጠረዥ 8 የሦስቱ ትምህርትቤት የግንዛቤ ሙከራ ሦስት የተማሪዎች ውጤት ........ 38

ሠንጠረዥ 9 የሦስቱ ግንዛቤ ሙከራዎች ጥቅል አማካይ የተማሪዎች ውጤት ........ 39

ሠንጠረዥ 10 ተጠኚ ተማሪዎች ጾታ፣ ዕድሜና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ........ 41

ሠንጠረዥ 11 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ንባብ ፍላጎት ከመፍጠር አንፃር ከተጠኚተማሪዎች የተገኘ መረጃ ........ 42

ሠንጠረዥ 13 የምንባቦችን ርዝማኔ በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ ........ 46

ሠንጠረዥ 12 ተማሪዎች ምንባቦቹን አንብበው መረዳት አለመረዳታቸውን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ........ 44

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004 ዓ.ም.በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ያላቸውን ተነባቢነት መፈተሽ ሲሆን ዝርዝር ዓላማውም ለተማሪዎቹ የንባብ ፍላጎት ተነሳሽነት ያላቸውን አስተዋፅኦ መመርመር እና አንብበው በበቂ ሁኔታ መረዳት አለመረዳታቸውን መለየት ናቸው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይረዳ ዘንድ ትምህርት ቤቶችና ምድቦች በተራ ዕጣ ናሙና እንዲሁም ተማሪዎችን ረድፋዊ አመራረጥ ስልት በመጠቀም ናሙና ተወስዷል። የምንባቦቹን ተነባቢነት ለመለካት የFlesch ቀመርና የFry ግራፍ ምንባብ መለኪያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል።ለተጠኚ ተማሪዎች የግንዛቤ ሙከራዎች /ፈተናዎች/ በመስጠት፣ ተማሪዎችን መጠይቅ በማስሞላትና ለመምህራን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ መረጃዎች ተሰብስበው በገላጭ እስታቲስቲክስ ዘዴ በመቶኛና በገለፃ ተተንትነው ቀርበዋል።የጥናቱም ግኝት እንደሚያመለክተው ምንባቦቹ ለክፍል ደረጃው ተነባቢነት የሌላቸውና በጣም ከባድ ከመሆናቸው የተነሳ ኮሌጅን ላጠናቀቁ ተማሪዎች የሚመጥኑ መሆናቸው የFlesch ቀመርና የFryግራፍ ትንተና ውጤት ያሳያል። በግንዛቤ ሙከራዎች / ፈተናዎች/ የተገኙ ውጤቶች ደግሞ የተማሪዎች የመረዳት ችሎታ መካከለኛ እንደሆነ አረጋግጧል። ለዚህ ምክንያት ሆነው የቀረቡት ምንባቦች ለቋንቋው ትምህርት በሚዘጋጁበት ወቅት በባለሙያዎች የተቃኙ በመለኪያነት የሚያገለግል ሥራ ላይ የዋለ መመዘኛ አለመኖር፣ የምንባቦቹ ቃሎች ከባድ መሆን የሚሉ ሲሆኑ ፤ከዚህም በተጨማሪ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ስለምንባቡ ፍንጭ በመስጠትና የንባብ ፍላጎት ለማሳደር የሚረዱ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ውይይት እንዲካሄድ አለማድረግ ፤ የተመደበው ክፍለጊዜ አነስተኛ መሆንና በቂ የልምምድ ጊዜ አለመኖር መሆናቸውን የተገኙ ምላሾች እና የተሰጡ አስተያየቶች አሳይተዋል ። በመጨረሻም የምንባቦችን ተነባቢነት ችግር ለማቃለል ያስችላሉ ተብለው ከታሰቡ አስተያየቶች ውስጥ ምንባቦች በሚዘጋጁበት ጊዜ ተነባቢነታቸውን ለመፈተሽ የክፍለትምህርቱ ባለሙያዎች እና ሌሎች ጥናት አድርገው በመለኪያነት የሚያገለግሉ መመዘኛዎች አገልግሎት ላይ ቢውሉ፣ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ውይይት የማድረግ ልምድ ቢጎለብት ፣ ምንባቦች ከመነበባቸው በፊት መምህራን ለአዳዲስ ቃላት ፍች ቢፅፉ፣ ተማሪዎች ስላነበቡት ነገር መልዕክቱን እንዲፅፉ መምህራን ቢያበረታቱ፣መምህራን ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚያደርጉት እገዛ ልዩ ትኩረት ቢሰጡ። እነዚህን ሀሳቦች በመሰንዘር ጥናቱ ተጠቃሏል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋትምህርትአላማበዋናነትአራቱንየቋንቋክሂሎችማለትምመናገር፣ማዳመጥ፣መፃፍናማንበብእንዲሁምየሥነልሳንናየሥነፅሑፍእውቀትንማጎልበትእንደሆነምሁራንአረጋግጠዋል(መሰሉ1994 ዓ.ም.፤ስዩም1994ዓ.ም.፤በድሉ1996.፤ፈቃደ1991 ዓ.ም.)።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የቋንቋ ትምህርት አላማዎች ግብ እንዲመቱና የተማሪዎችን ችሎታ ለማጎልበት በየክፍል ደረጃ የተዘጋጁ የመማሪያ መፃሕፍት መኖር ተገቢ ነው። ስለሆነም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚዘጋጁ መፃሕፍት በክፍል ደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን የሚመጥኑና ክሒሎቻቸውን እንዲያጎለብት የታሰበበት ሊሆን ይገባል። ይህንን አስመልክቶ ጌታቸው (1986ዓ.ም.፣ 2-3) አያሌው (1985 ዓ.ም.)እና አስፋው (1975 ዓ.ም.)ን በመጥቀስ እንዳብራሩት ፣

> *በ1970 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ማስተማሪያመፅሐፎች ተዘጋጅተው ይቅረቡ እንጂ ጥራታቸውና ለተመደቡበት የክፍል ደረጃ የማይመጥኑ፣ የቋንቋ ክሒሎችን ለማዳበር ከማስቻል አንፃር ሲታይ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ ክፍል የተገኙ መረጃዎች በአዎንታዊነት መልክ እንደማያመለክቱ እና ከተማሪው ልምድ ጋር የማይጣጣሙ፣ በመሆናቸው የአማርኛ ትምህርት፣ በተማሪዎቹ እንዲጠላ ማድረጉን ገልፀውታል።*

ከላይ ከተብራራው ሃሳብ የምንረዳዉ በወቅቱ የነበረው የማስተማሪያ መፅሐፍ ታስቦበት ያልተዘጋጀ እና ለክሒሎች እንዲሁም ለሥነፅሑፍና ሥነ-ልሳን እውቀት መጎልበት አስተዋፅኦ እንደሌለው የክፍል ደረጃውን የማይመጥን፣በጥናት እንደተረጋገጠውም ከተማሪዎቹ ችሎታ በላይ መሆኑ በትምህርቱ ላይ ጥላቻ እንጂ ተነሳሽነትን የማይጋብዝ መሆኑን ነው።

ይሁንእንጂ እንደ ወንድወሰን (2000ዓ.ም.፣2) ናርዶስናሐሰን(1998)ን ጠቅሰው እንደገለጹት፣

> *«በ1986ዓ.ም.አዲሱየኢትዮጵያትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ከወጣ ወዲህ በትምህርት ሴክተሩ በርካታ ለውጦች መካሔዳቸውን አስረድተዋል።ይህም የሥርዓተ ትምህርቱ መለወጥ አጠቃላይ የትምህርት አቅጣጫውን፣ ሀገራዊ የትምህርት ግቡን፣ የትምህርት ይዘቱን፣ የትምህርት ደረጃና እርከኑን፣ የማስተማሪያ ዘዴዉን ፣የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውኑን፣ የግምገማ ስልቱን፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅቱንአዲስ መልክ እንዲይዝ አድርጎታል።»*

በመሆኑም ተማሪው እውቀቱን የሚቀዳበት ባህር ዋነኛው መሣሪያ መማሪያ መፅሐፍ ስለሆነ፣ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ፅንሰ ሃሳቦች የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ተማሪው መረዳት የሚችለው እና ባነበበው በተማረው ሊጠቀምበት የሚችል መሆን አለበት።

የቋንቋ ትምህርትም ትምህርቱ ከሚተላለፍበት አንዱ መንገድ ለተማሪዎች በምንባብነት በሚቀርበው ፅሑፍ ነው። በምንባብ አማካኝነት የማንበብ ክሂላቸውን ያጎለብቱበታል ፤ በምንባብ ውስጥ የሚገኙትን አባባሎች፣ አዳዲስ ቃሎችንና ፅንሰ ሃሳቦችን ይማሩበታል፤ ያነበቡትን መረዳት ሲችሉ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መስራት እና የክፍል ውስጥ ተሳትፎም እንዲጨምር አስተዋፅኦ ያደርጋል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ምንባቡ ተነባቢነት ሲኖረው ነው።

ተነባቢነት በተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍ ላይ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቦታ የሚቀርብ ፅሑፍ ተነባቢነት ሊኖረው እንደሚገባ እና ፅሑፉ ተነባቢነት ከሌለው (አንባቢው አንብቦ በቀላሉ መረዳት ካልቻለ) መመሪያ ያለውን አንድን ነገር ለመጠቀም ችግር እንደሚገጥመው ወይም አንብቦ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያዳግተው የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ። ለምሳሌ፣ DuBay (2004፣2)

> *"እንደ ብሔራዊ የጤና ማዕከል ዘገባ በ1998 ጎልማሶች ከአደጋ መከላከያ መቀመጫ መመሪያን አንብበው መረዳትና አጠቃቀሙን ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻላቸው ዕድሜያቸው 1-14 ዓመት የሚገኙ ህፃናት ህይወታቸው አልፏል። ፀሐፊው ማሳየት የፈለገው በአሜሪካ አብዛኛዎቹ*

*ጎልማሶች የትምህርት ደረጃቸው 7ኛ ክፍል መሆናቸውና የዚህ መመሪያ አማካይ የተነባቢነት ደረጃ ለ10ኛ ክፍል በመሆኑ መልዕክቱን አንብበው መረዳት አለመቻላቸውን ነው። በመሆኑም ፅሑፉ 80% ለሚሆኑ የአሜሪካ ጎልማሶች በጣም አስቸጋሪ ወይም ከደረጃቸው በላይ እንደሆነ አንብበው እንደማይረዱት ገልፀውታል።"*

ከፅሑፉ የምንረዳዉ የምናነበው ፅሑፍ እና የክፍል ደረጃችን ተመጣጣኝ ካልሆነ በንባብ አማካኝነት ነገሮችን ተረድቶ ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ነው። ተነባቢነትን አስመልክቶ የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ሀገር ምሁራን የተለያዩ ሃሳቦችን ሠንዝረዋል።

Williams (1984) ተነባቢነት ምንባቡ የቀረበበት ቋንቋ ለክፍል ደረጃው ግልፅ እና ይዘቱ ተሰማሚነት ኖሮት የንባብ ፍላጎትን የሚያሳድር ከሆነ ፅሑፉ ተነባቢ ነው። ስለዚህ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውል ምንባብ የቀረበበትን ቋንቋ ለክፍል ደረጃዉ ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን ፣የይዘት ተስማሚነቱንና የንባብ ፍላጎት ማሳደሩን የምንመረምርበት/የምንለካበት መሆኑን ያስገነዝባሉ።

እንዲሁም ፍቃዱ (1995 ዓ.ም.፣13)ድሬየር (1984)ን በመጥቀስተነባቢነት ለንባብ የቀረበው ጽሑፍ በቀላሉ ሚነበብ ፣ አንባቢውን የማስደሰት ኃይል ያለውና አንብቦ ለመረዳት አንባቢው የማይቸገር ከሆነ ወይም እነዚህን ሁለቱንም በአንድነት የሚያሟላ ፅሑፍ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሳቦች የምንረዳው አንባቢው ከፅሑፍ ጋር በሚያደርገው መስተጋብር ሳይቸገር የሚያነበው ሃሳብ በቀላሉ መረዳት የሚችለው፣ የንባብ ፍላጎት የሚያሳድር እና ፅሑፉ አንባቢውን የማስደሰት ሃይል ያለው ምንባብ ተነባቢ ነው።ከዚህም ሌላ የአንድን ፅሑፍ ተነባቢነት የሚጎዱ እንደ ፊደል ግድፈት ፣የፊደሎቹ መጠን (ትልቅነትና ትንሽነት) ፣ የህዳግ ና የፍኖት በአግባቡ አለመጠበቅ መሆናቸውን ከምሁራኑ ሃሳብ ተረድተናል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር

በ2004 ዓ.ም.(ዓመተ ምሕረት)በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች የቋንቋውን ክሒሎች ያጎለብታሉ ተብለው የታሰቡ እና የተነባቢነት ጉድለት እንደሌለባቸው፤ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ ግልፅና ሳቢ እንዲሆኑ ጥረት መደረጉን እንደዚሁም ሌሎች ክፍሎቹ መልመጃዎችን ጨምሮ የትምህርቱን አላማዎች ለመጨበጥ ያስችላሉ ተብለው መታመኑን በመግቢያው ላይ ይዘረዝራል፡፡ይሁን እንጂ ምንባቦቹ ሲመረጡ ተነባቢነታቸው በምን መንገድ እንደተፈተሸ የሚያስረዳ ሃሳብ የለም፡፡በመሆኑም በዚሁ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተነባቢነት ምን ያህል እንደሆነ የመረመረ ሥራ ባለማግኘቷ ጥናቱን ለማካሔድ ካነሳሷት ምክንያቶች ቀዳሚው ነው፡፡

በማስተማር ዓለምም ለረጂም ጊዜ በቆየችባቸው ጊዜያት ክፍል ውስጥ በትምህርቱ ሒደት በንባብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የምንባቦችን ፅንሰ ሀሳብ ለመረዳት ሲቸገሩና ምንባቦችን በተመለከተ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ለመስጠት ሲያዳግታቸው በመመልከቷ ምናልባት ይህ ችግር ምንባቦቹ ለተማሪዎች ደረጃ አይመጥን ይሆን የሚል ጥያቄ ስለፈጠረባት ጥናቱን ለማድረግ ያነሳሳት ሌላው ምክንያት ነው፡፡ በተጨማሪም አጥኚዋ ከላይ በተገለጸው መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን ተነባቢነት የፈተሸ ጥናት ያላጋጠማት መሆኑም ለጥናቱ መደረግ ሌላው ምክንያት ሆኗታል፡፡

በመሆኑም ጥናቱ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ያስገኛል ተብሎ ታስቧል፤

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ተነባቢነት አላቸው?
- የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ፍላጎት ተስማሚ ናቸው?
- ተማሪዎቹ ምንባቦቹን አንብበው በበቂ ሁኔታ ይረዱታል?

## 1.3 የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህጥናት ዋና አላማ በ2004 ዓ.ም በታተመውበ10ኛ ክፍልየአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ያላቸውን ተነባቢነት መፈተሽ ነው፡፡ ከአጠቃላይ አላማው በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፤

1. በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃዉ ያላቸውን ተነባቢነት መፈተሽ፤
2. ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ የንባብ ፍላጎት ተነሳሽነት ያላቸውን አስተዋጽኦ መመርመር፤
3. ተማሪዎቹ ምንባቦቹን አንብበው በበቂ ሁኔታ መረዳት አለመረዳታቸውን መለየት፤

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፤

1. የመማሪያ የማስተማሪያ መፅሐፍ አዘጋጆች ምንባብን ለማስተማሪያነት ሲመርጡ በምን መስፈርት መምረጥ እንደሚኖርባቸው ሃሳብ ይሰጣል፤
2. በክፍል ደረጃውየሚገኙ ተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት ከማጎልበት አንጻር የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ ምን መሆን እንዳለበት ለሥርዓተትምህርት ባለሙያዎች ይጠቁማል፤
3. በምንባቦች ተነባቢነት ላይ ወደፊት ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ (ለሚያስቡ) ሰዎችእንደመነሻ ያገለግላል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በ2004 ዓ.ም በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑምጥናቱ በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ተነባቢነት ከመፈተሽ ውጪ ሌሎች ጉዳዮችን (የመምህራን የማስተማር ዘዴ ሥልጠናና ብቃት፤የመልመጃዎችን አደረጃጀት ተገቢነት) አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2-1 ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የተነባቢነት ምንነት

“የሰው ልጅ ስለአካባቢው ብሎም ስለአለም ያለውን ግንዛቤ የሚያሰፋው እውቀቱን የሚያጎለብተው ስሜት የሚኖረው፣ የጨበጠውንና ያካበተውን የሚያዳብረው፣ የነገሮችን ምስጢር የሚመረምረው፣ ሃሳብን ለማመዛዘን ችግሮችን ለመፍታት እና የአስተሳሰብ ብቃትን ለማግኘት ንባብ ወሳኝነት አለው ”( ወንድወሰን2004 ዓ.ም.፤2):: ይሁን እንጂ ይህን ከላይ የተገለፀውን ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው ያነበበውን ምንባብ በቀላሉ መረዳት ሲችል ነው። መረዳት የሚኖረው ደግሞ ፅሑፉ ለአንባቢው ተነባቢነት ሲኖረው ነው።ከዚህ መሠረታዊ ወሳኝ የንባብ ጠቀሜታ ለመጋራት በአግባቡ ለመጠቀም የአንድ ፅሑፍ ተነባቢነት ምን እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው።

ተነባቢነትየአንባቢን ስሜት ወጥሮ በመያዝ አንባቢን ያለምንም መሰላቸት ከገፅ ወደገፅ የሚያሸጋግር ፣ሥራው ሳቢ ፣ከባድ ቃላት ያልበዛበት ፣ ከተማሪዎች ችሎታ ባልበለጠ ቋንቋ የቀረበ እንዲሁም ሀሳቡን በቀላሉ ለመረዳት የማያዳግት እና የንባብ ችሎታን ለማጎልበት አስተዋፅኦ ያለው ነው።ስለዚህም ምንባቦችን የመገምገሚያና የመምረጫ ዘዴዎች አንዱ ተነባቢነት በመሆኑ ምንባብ ተነባቢነት እንዲኖረው ለማንበብ ተነሳሽነትን መፍጠር እንዳለበት ያስገነዝባሉ ( Nuttal 1982)።

እንደNuttal(1982) አገላለፅ ተነባቢነት አንባቢውን ከገፅ ወደ ገፅ በጉጉት የሚያሸጋግርና ሃሳቡንም በቀላሉ ለመረዳት የማያስቸግር በሒደቱም የአንባቢውን የንባብ ክሒል ለማጎልበት አስተዋፅኦ ያለውእና ምንባቦችን ለማዘጋጀት መምረጫ መንገድ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

እንዲሁም DuBay(2004፣3) ተነባቢነትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራንን ሃሳብ እንደሚከተለው አስፍረውታል።

- Hargis and IBM (1998) ተነባቢነት ለምንባብነት የቀረበን ፅሑፍ ቃላቱንና ዐረፍተ ነገሩን በቀላሉ ማንበብ፣ መረዳት ፣ሀሳቡ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ሠርፆ መቅረት እንዲሁም ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ በቀላሉ መስጠትን የሚያመለክት ሲሆን፤ ይህም የፅሑፉ (የምንባቡ ) ሀሳብ ግልፅ መሆን መገለጫው መንገድ ነው።
- Mclaughlin (1969) የ SMOG ቀመር መስራች የሆኑት ሥራው የቀደመ እውቀቱን ያገናዘበ ሆኖ በተማሪውና በፅሑፉ መካከል በሚኖረው መስተጋብር ተማሪው በምንባቡ ሳቢነት የተነሳ ትኩረት ሰጥቶ በማንበብ መረዳት ያነበበውን መተረክ ፣ የንባብ ክሒሉን የሚያጎለብትና ለንባብ ፍላጎት ተነሳሽነትን የሚፈጥር ነው።

- Dale and chall's (1949) ተማሪው በንባብ ስኬታማ እንዳይሆን ተፅእኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች መካከል ምንባቡ በአዳዲስ ቃላት የታጨቀ መሆን እና የዐረፍተ ነገር መርዘም ናቸው።ውጤቱም ተማሪው ምንባቡን አለመረዳት ፣መሰላቸትና የንባብ ፍላጎትን ማሳጣት ነው። ስለዚህ ተነባቢነት በንባብ ስኬታማ መሆንን ፣ ምንባብ በሚፈለገው ፍጥነት ማንበብ፣ መረዳት ነው።

ከላይ ከተገለፁት የተለያዩ ምሁራን ሀሳብ የምንረዳው ተነባቢነት በምንባብነት የቀረበን ፅሑፍ በቀላሉ ማንበብ ፣መረዳት፣ለጥያቄ በቂ ምላሽ መስጠት የሚያስችለውና ለንባብ ፍላጎት ተነሳሽነትን የሚፈጠር ሲሆን፤ምንባብን አለመረዳት ፣መሰላቸት ና የንባብ ፍላጎት እንዳይኖር ከሚያደርጉ ሁኔታዎች መካከል ምንባቦች በአዳዲስ ቃላት መታጨቅና የዐረፍተ ነገሮች መርዘም ናቸው።

Alderson (2001፣70-76) በበኩላቸው አንባቢው ከፅሑፉ ጋር በሚፈጥረው መስተጋብር ስኬታማ የሚሆነውና እውቀት የሚያገኘው የሚመጥነውን ፅሑፍ ሲያገኝ ነው። የሚመጥነውን ምንባብ ማግኘቱ የሚገለፀው ፅሑፉን ተገቢ በሆነ ሁኔታ ማንበብ፣ በቀላሉ መረዳት፣ ባነበበው መሠረት ለጥያቄ መልስ መስጠት

እና የንባብ ፍላጎትን የሚያሳድግ ሲሆን ነው። ሆኖም ፅሑፉ ከደረጃ በላይ ከሆነ ፍላጎት በማጣት ንባቡን ያቆማል። በሌላ በኩል ብቁ ችሎታ ያለው አንባቢ ፅሑፉ ከደረጃዉ በታች ከሆነ በንባብ ለመግፋት ደስተኛ አይሆንም። አያይዘውም Larson(1984፣499-500) ‹‹ተነባቢነት እንዳይኖረው ይዘቱ የቀረበበት ቋንቋ ደረጃ ብቻ ሳይሆን የፊደሉ መጠን (Font)፣ የፊደል ግድፈት፣ የህዳግ ናየፍኖት መጥበብ እንዲሁም ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ አለመጠቀም የመሳሰሉ ጉዳዮች ተነባቢነት እንዳይኖር ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ያብራራሉ።››

Larson (1984) አክለውም ሲያስረዱ ምንባብ ተነባቢ ነው ለማለት የሃሳብ አገላለፁ፣ የቃላት አመራረጡ፣ የሃሳቡ አለመቆራረጥ፣ አንባቢን የሚያስደስት እና የሃሳብ ፍሰቱን የጠበቀ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ መረሳት የሌለበት ለአንዱ ተነባቢ የሆነ ፅሑፍ ለሌላው ተነባቢ ላይሆን ይችላል። ማለትም አንዱ አንባቢ ፅሑፉን አንብቦ በቀላሉ የተረዳውን ሌላው አንባቢ እስከነጭራሹ ላይረዳዉ ይችላል። ስለዚህም የምንባቦችን ተነባቢነት በመፈተሽ ሒደት ውስጥ የትኛው ምንባብ ለየትኛው ደረጃ ተስማሚ እንደሆነ መለየት ያስፈልጋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳብ የምንረዳው ምንባብ ተነባቢነት እንዲኖረው የሀሳብ አገላለፁ፣ የቃላት አመራረጡ ፣የሀሳብ ፍሰቱን ጠብቆ ለአንባቢው የሚፈለገውን ሀሳብ በማስተላለፍ እውቀት የሚያስጨብጥና ባነበበው ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ መሆን አለበት ። ይሁንእንጂ የቃላት አመራረጡና የሀሳብ አገላለፁ የተዋጣ ቢሆንም እንኳን የፊደል ግድፈት ፣የህዳግና የፍኖት መጥበብ እንዲሁም ተገቢ ሥርዐተነጥብ በተገቢ ቦታ አለመቀመጥ አንባቢው ፅሑፉን እንዳይረዳው አስተዋፅኦ አላቸው። መረሳት የሌለበት ከላይ የተጠቀሱት ዝርዝር ጉዳዮች ተስተካክለው ቢቀርቡም ለአንዱ ተነባቢ የሆነ ፅሑፍ ለሌላው ተነባቢ ላይሆንይችላል እና ለየትኛው ደረጃ ተስማሚ እንደሆነ መፈተሽ ያስፈልጋል።

እንዲሁም Berhe(1989፣12)klare(1963)ን በመጥቀስ በትምህርት ቤቶችም ሆነ በተለያዩድርጅቶች ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችግር ይታያል።ስለዚህ የምንባቦች(ፅሑፎች)ን ደረጃ ለመፈተሽና ተስማሚነቱን ለመለየት ችግሩን ለማቃለልየተነባቢነት ቀመር መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝቡናል።

## 2.2 የተነባቢነት ቀመሮች

በ1920ዎቹ፣ምሁራን የአንድን ፅሑፍ የተነባቢነት ደረጃ ለማወቅ፤ የቃሉን ክብደትና የዐረፍተ ነገሩን ርዝመት ለመመርመር የሚያግዙና የምንባቦችን የተነባቢነት ደረጃ ለመለየት የሚያስችሉ የተነባቢነት ቀመሮችን መሠረቱ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነዚህ የተነባቢነት መለኪያ ቀመሮች የተለያዩ ጥናቶችና መሻሻሎች እየተደረገባቸው በስራ ላይ ውለዋል፡፡የተነባቢነት ቀመሮቹ የሒሳብ ስሌቶችን መሠረት በማድረግ አንድ ፅሑፍ ለየትኛው የክፍል ደረጃ ተመጣጣኝነት ኖሮት ተነባቢ እንደሆነ ለመለየት የሚያገለግሉ የመገምገሚያ መሳሪያዎች ናቸው (Zamanian 2012፣44፤DuBay 2004፣2-3)፡፡

Vacca and Richard (1998፣155) Hittleman (1973) ን ጠቅሰው እንደገለፁት የተነባቢነት ቀመር የሚሰራው በሌላ ምንባብ ላይ ያለውን የተማሪውን እውቀትና ልምድ ሳይሆን በዚያው ቅፅበት በቀረበው ምንባብ ላይ የሚገለፀውን ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ቀመሩን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ምንባብ ለተማሪው አንብቦ የመረዳት፣ ሳነበበው ሃሳብ ማጠቃለያ የመስጠት አቅሙን ያጎለብትለታል፡፡ እንዲሁም ለመምህሩ የተማሪውን ስሜት፣ የመረዳት አቅም፣ የቋንቋ ዳራውንና ፍላጎቱን እንዲገመግም ይረዳዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች የምንረዳው የተነባቢነት ቀመሮች መቼ እንደተመሰረቱ፤በየጊዜው መሻሻሎች ተደረጎባቸው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን እና ቀመሮቹምንባቦች(ፅሑፎች) ለየትኛው ክፍል ደረጃ ተመጣጣኝ እንደሆኑ ለመለየት ያገለግላሉ፡፡ስለዚህየተነባቢነት ቀመሮችን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ምንባቦች (ፅሑፎች) ለተማሪው አንብቦ የመረዳት ችሎታን እዲያጎለብት፤ ለመምህሩም ተማሪውን ለመገምገም ይረዳዋል፡፡

"የተነባቢነት ቀመሮች አለምአቀፋዊ ስምምነት ያላቸውና ውጤታማ ቢሆኑም አከራካሪና ድክመት እንዳለባቸው"( DUBay 2004፣2)ጠቁመዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የቀመሮቹን ጥቅምና ጉዳት አስመልክቶ Zamanian (2012፣48)እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡‹‹የተነባቢነት ቀመርምንባቡ (ፅሑፉ)ተማሪው ባለበት ደረጃ እንዲዘጋጅ እገዛ ስለሚያደርግ ተማሪው በደረጃው የተዘጋጀለትን የመማሪያ

መፅሐፍ እንዲያነብ እንዲሁም መመሪያዎችን አንብቦ ተግባራዊ በማድረግ ለመጠቀም ትልቅ እገዛ ከማድረጉም ሌላ ፅሑፉን በማየት ብቻ ከባድ ወይም ቀላል ነው በማለት እንዳይወሰን ይረዳል፡፡"

ይሁንእንጂ የተነባቢነት ቀመሮች ጥቅም ብቻ ሳይሆን ጉዳትም አላቸው ፡፡የተለያዩ የተነባቢነት ቀመሮች አንደመኖራቸው በተመሳሳይ ፅሑፍ በተለያዩ ቀመሮች ተሰልቶ የሚገኘው ውጤት ልዩነት አለው፡፡ ይህም ማለት አንድ ምንባብ በተለያዩ ቀመሮች ሲለካ ውጤቱ የተለያየ ይሆናል ማለት ነው፡፡በተጨማሪ የተነባቢነት ቀመር የቀደመ እውቀትን ፣የፍላጎት ደረጃን ፣የሀሳብ ውስብስብነትንና የፅሑፍ ተለጣጣቂነትን አይለካም፡፡

ከነዚህ ሃሳቦች በመነሳት የሚከተሉትን የማጠቃለያ ሃሳቦች Vacca and Richard (1998፣155-156) አቅርበዋል፡፡

> *በትምህርቱ ዙሪያ አንብቦ መረዳትን ማበረታታት፣ተማሪዎች የቤትሥራቸውን እንዲሰሩ የሚያግዛቸውን መመሪያ መስጠት፣በንባብና በውይይት ጊዜም አዳዲስ ሀሳቦችን አጉልቶ ማሳየት በእጅጉ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል፡፡ስለዚህ ምንባብን ለመገምገም ቀላል የተነባቢነት ቀመር እንደ ድጋፍ ለመጠቀም መማር ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም በንባብ ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ ሌሎች ሁኔታዎች ለምሳሌ የአካባቢ ፀጥታ መታወክ እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡*

ከላይ ከተገለፁት ሀሳቦች የምንረዳው ምንባቦች በሚዘጋጁበት ጊዜ ቀመሮቹ ላይ ብቻ መወሰን ሳይሆን የተማሪውን ልምድ፣ደረጃና አውድ ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚያስፈልግ፣በንባብ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ሌሎች ሁኔታዎችን ለምሳሌ የአካባቢ ፀጥታ መታወክ እና በቀመሩ መጠቀም መማር ማስተማርን ሂደት ማይተካ መሆኑን ነው፡፡

ከVacca and Richard (1998) ምክር ጋር በሚመሳሰል መልኩ DuBayም(2004፣2) እንዳብራሩት የመስኩ ባለሙያዎች በጥናታቸው እንዳስፈሩት ፅሑፋችን ተነባቢነት እንዲኖረው ለሚከተሉት ወርቃማ ህጎች ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ፡፡

- ምንባቡ በአዳዲስ ቃላት ያልታጨቀ ፣የተወሰኑ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ብቻ የሚያግባቡ መሆን እንደሌለባቸው እንዲሁም ከባህልና ከፆታ ተፅዕኖ ነፃ ለሆኑ ቃላት ትኩረት በመስጠት ቀላልና የተለመዱ ቃላትን መጠቀም፤
- ተማሪው (አንባቢው) እንዲተገብረው የተፈለገውን ድርጊት፣ሀሳብ፣ መመሪያው ሁሉም እንዲረዳው የማያሻማና ግልፅ አድርጎ መፃፍ፤
- የሰዋሰው፣ የሥርዓተነጥብ እና የፊደላት ግድፈት እንዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ በተጨማሪ ትኩረት እንዲሰጣቸው ለሚፈለጉ ሀሳቦች ና ምልክቶች የተለያየ አቀማመጥ እና የፊደል አጣጣል መጠቀም፤

ከላይ የተገለፁት ማሳሰቢያዎች እንደተጠበቁ ሆነው በርካታ የተነባቢነት ቀመሮች ንባብ ደረጃ ከመወሰን አንጻር ጠቀሜታቸው የጎላ በመሆኑ ቀደም ሲል በሥራ ላይ መዋላቸውንና በቀጣይነትም ጥቅም ላይ መዋል እንደሚገባቸው(Vacca and Richard 1998፣157)ያስገነዝባሉ።

ከነዚህ የተነባቢነት ቀመሮች ውስጥ Flesch(1949)፣Dale and chall(1967)፣ Gunning'sFog(1952)፣ MClaughlin's SmOG(1969)፣Fry(1977)፣ Gilliland(1972) እና Browns(1998) ለቋንቋ ማስተማሪያ ምንባብ መምረጫነት ሲያገለግሉ የቆዩና የታወቁ ቀመሮች እንደሆኑ የመስኩ ባለሙያዎች (Nasser2014፣2046፤DuBay2004፣20-42)ያስገነዝባሉ።

### 2.2.1 የFlesch (1949) ቀመር

Flesch(1949) ቀመር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ና ለሁለተኛ ደረጃ ምንባቦች ተነባቢነት መለኪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው።ቀመሩን ተግባራዊ በማድረግ በስሌት በሚገኘው ውጤትምንባቡ ለየትኛው ክፍል ደረጃ እንደሚገመት መረዳት ይቻላል።

ቀላል የንባብ ነጥብ = 206.835-(1.015xASL)-(84.6xASW)

ASL = አማካይ የዐረፍተነገር ርዝመት (የቃላት ብዛት ሲካፈል ለዐረፍተነገር ብዛት

ASW = በቃል ውስጥ የሚገኝ አማካይ የቀለም ብዛት (የቀለም ብዛት ሲካፈል ለቃላት ብዛት)

Zamanian( 2012፣45)እና DuBay (2004፣21) (Chall 1958፣Klare 1963)ንበመጥቀስይህቀመርበስፋትአገልግሎትላይየዋለናተቀባይነትያገኘዛሬምድረስለ ሁለተኛደረጃበተነባቢነትቀመርእያገለገለያለመሆኑንይገልፃሉ።

ይሁን እንጂ DuBay(2004 21-22) እንዳብራሩት Farr, Jenkins, Paterson (1951) ያሻሻሉትን Flesch ቀመር መጠቀም እንደሚገባ አስረድተዋል፡:

ቀላል የንባብ ነጥብ =1.599 nosw - 1.015.sl -31.517

nosw= በ100 ቃላት ውስጥ የሚገኙ ባለአንድ ቀለም ቃላት ብዛት

Sl = የዐ.ነገር ርዝመት (የቃላት ብዛት ሲካፈል ለዐረፍተነገር ብዛት)

የ Flesch ቀመርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ሒደቶች መከተል ያስፈልጋል።

1. ሦስት ባለ 100 ቃሎች ምንባቦችን ከመፅሐፉ መጀመሪያ፣መካከልናመጨረሻላይ መውሰድ

2 በ100 ቃሎች ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን መቁጠርና አማካይ ማውጣት

3 በ100 ቃሎች ውስጥ የሚገኙ ዐረፍተነገሮችን መቁጠርና አማካይማውጣት

4 ቀመሩን ተግባራዊ ማድረግ (ወደ ስሌቱ መግባት)

DuBay (2004፣22)፤Nasser(2014፣2046)፤Zamanian(2012፣45) የ Flesch ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥን እንደሚከተለው አሰቀምጠዋል።

ሠንጠረዥ 1የFlesch(1949) ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥ

| የንባብ ቅለት ነጥብ | የምንባቡ ክብደት የተገለፀበት ዘዴ | ምንባቡ የተገመተው ክፍል ደረጃ |
|---|---|---|
| 0-29 | በጣም ከባድ | ኮሌጅን ያጠናቀቁ |
| 30-49 | ከባድ | ከ13ኛ-16ኛ ክፍል |
| 50-59 | በመጠኑ ከባድ | ከ10ኛ-12ኛ ክፍል |
| 60-69 | መጣኝ | 8ኛ እና 9ኛ ክፍል |
| 70-79 | በመጠኑ ቀላል | 7ኛ ክፍል |
| 80-89 | ቀላል | 6ኛ ክፍል |
| 90-100 | በጣም ቀላል | 5ኛ ክፍል |

ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ የምንረዳው የFleschቀመር ምንባብን መለኪያ ዘዴዎች አንዱና በስፋት አገልገሎት ላይ መዋሉን ነው፡፡እንዲሁም ቀመሩን ተግባራዊ ለማድረግ መከተል የሚያስፈልገውን ሒደቶች እና የሚገኘውን ነጥብ (ውጤት) ሠንጠረዡ ላይ ከሚገኘው የንባብ ቅለት ነጥብ ጋር በማገናዘብ የክብደት ደረጃና ምንባቡ ለየትኛው ክፍል ደረጃ እንደተገመተ ያሳያል፡፡

### 2.2.2 የEdward Fry (1977) ግራፍ

Edward Fry በ1977 የወጣው የተነባቢነት ግራፍ ቀላልና ፈጣን ሲሆን ከአንደኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ለሚገኙ የተነባቢነት መለኪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ Fry ግራፍ ለመጠቀም የሚከተሉትን መመሪያዎች ተግባራዊ በማድረግ ፅሑፉ ለየትኛው የክፍል ደረጃ እንደሚመጥን መገመት ይቻላል፡፡

1. ሶስት ባለ 100 ቃላት ምንባቦችን ከመፅሐፉ መጀመሪያ መካከልና መጨረሻ መውሰድ
2. በሶስቱም ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን ዐረፍተነገሮች ብዛት መቁጠር፣ ከ100 ቃላት በላይ የሆነውን የመጨረሻውን ዐረፍተነገር ወደ 1/10ኛ ማጠጋጋት
3. በሶስቱም ናሙና ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን ዐረፍተነገሮች ብዛት ደምሮ አማካይ ማውጣት

4. በሶስቱም ናሙና ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን ቀለሞች መደመርና አማካዩን ማውጣት
5. የዐረፍተነገሮችን አማካይ ውጤትና የቀለሞች አማካይ ውጤት በግራፍ ላይ ማመልከት
6. ሁለቱ ውጤቶች የሚገናኙበት ቦታ ላይ ነጥብ (.) ማድረግ፤ይህም ሁለቱ የሚገናኙበት ቦታ ግምታዊ የክፍል ደረጃን ያመለክታል(Nuttall 1982፣ 27፤ Vacca andRichard1998 ፣ 156-157) ፡፡

በአጠቃላይ Fry ግራፍ ለዐረፍተነገርብዛትናለቀለሞች ብዛትትኩረትይሰጣል፡፡ በመሆኑም የዐረፍተነገር ብዛት በአማካይ ለማግኘት በእያንዳንዱ ናሙና ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ዐረፍተነገሮችን ብዛት መቁጠርና የሦስቱን ናሙና ምንባቦች ዐረፍተነገሮች ብዛት ደምሮ ለሦስት በማካፈል አማካይ የዐረፍተነገር ብዛት ይገኛል፡፡እንዲሁም የቀለሞች ብዛት በአማካይ ለማግኘት፤ በሦስቱም ናሙና ምንባቦች በ100 ቃሎች ውስጥ የእያንዳንዱን ናሙና ምንባብ ቀለሞች መቁጠር ከዚያም የሦስቱን ናሙና ምንባቦች ቀለሞች መደመር እና ለሦስት በማካፈል አማካይ የቀለም ብዛት ይገኛል፡፡በመጨረሻም የዐረፍተነገሮችና የቀለሞች አማካይ በግራፍ ላይ በማመልከት ሁለቱ የሚገናኙበት ቦታ የተገመተውን ክፍል ደረጃ ያመለክታል፡፡

### 2.2.3 የGunning'sFog(1952) ቀመር

እንደDuBay(2004፣23) አገላለፅ በጋዜጦች እና በንግድ ሥራ ፅሑፎች ላይ የሚታየውን የተነባቢነት ችግር ለመቅረፍ የተዘጋጀ ነው፡፡ቀመሩን ተግባራዊ ለማድረግ ሁለት ሃሳቦችን ተጠቅሟል፡-

1/ አማካይ የዐረፍተነገር ርዝመት

2/ ከባድ ቃላት

የንባብ ቅለት ነጥብ = 0.4 (አማካይ የዐረፍተነገር ርዝመት + ከባድ ቃሎች)

አማካይ የዐረፍተነገር ርዝመት = የቃሎች ብዛት ሲካፈል ለዐረፍተነገር ብዛት

ከባድ ቃላት = ከሁለት ቀለም በላይ ያላቸው ቃሎች ብዛት

ሠንጠረዥ 2 የGunning'sFog(1952)ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥ

| የንባብ ቅለት ነጥብ | ምንባቡ የተገመተለት የክፍል ደረጃ |
|---|---|
| 13-17 | ኮሌጅበመማር ላይ ላሉ እና ላጠናቀቁ |
| 9-12 | ከ9ኛ-12ኛ ክፍል |
| 8 | 8ኛክፍል |
| 7 | 7ኛ ክፍል |
| 6 | 6ኛክፍል |

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው Gunning'sFog ቀመር በመማሪያ መፃሕፍት ላይ ሳይሆን ጋዜጦችንናየንግድ ሥራ ፅሑፎችን ለማዘጋጀት የሚረዳ ነው፡፡በመሆኑም ቀመሩን በመጠቀም በስሌት የሚገኘውን ውጤት ሠንጠረዥ ላይ ከሠፈሩት ነጥቦች ጋር በማነፃፀር ፅሑፉ ለየትኛው ክፍል ደረጃ ተነባቢነት እንዳለው መገመት እንደሚቻል ይገልፃል፡፡

### 2.2.4 የማንዛቤ ዝግ ሙከራ/CloZe Test/ Wilson Taylor (1953)

የግንዛቤሙከራ ተማሪዎች ከአንድ ምንባብ ጋር በሚፈጥሩት መስተጋብር ምንባቡን ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ ይረዳል፡፡ ምክንያቱም ምንባቡ ለእዚያ ክፍል ደረጃ ተነባቢነት ሲኖረው ተማሪው ያነበበውን መገንዘብ ይችላል፡፡የግንዛቤ ሙከራ ጥያቄ የሚዘጋጀው 100ቃላት የያዙ ሦስት ምንባቦች ከመማሪያ መፅሐፉ መጀመሪያ ፣ መካከልና መጨረሻ በመውሰድ የየምንባቡን የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር በመተው እና ከሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ጀመሮ አራት ቃላትን ቆጥሮ አምስተኛውን ክፍት በመተው መዘጋጀት ይኖርበታል፡ በአጠቃላይ ከየምንባቡ 50 ክፍት ቦታዎችን ማዘጋጀቱ ተአማኒነቱን ይጨምራል፡፡ የሚገኘው ውጤት ማነስ ተማሪው ምንባቡን እንዳልተረዳዉ ሲገልፅ በተቃራኒው ጥሩ ውጤት የሚገልፀው ምንባቡን እንደተረዳው ነው(Alderson2001፣207፤Clark1986፣293-294፤DuBay2004፣26-27.፤Wallace1993፣77፤Vacca andRichard1998፣156፤Arthur 1992፣62)፡፡

የግንዛቤ ሙከራ አሰጣጥን አስመልክተውVacca and Richard (1998፣158)የሚከተሉትንአካሔድ መከተል ጠቃሚ እንደሆነ ያስረዳሉ፤

- የፈተናውን አላማ ለተፈታኝ ተማሪዎች ማሳወቅ፤
- በሚሰሩበት ጊዜ መፅሐፉን መጠቀም እንደሌለባቸው ሆኖም ከመፈተናቸው በፊት እንዲያነቡት መንገር፤
- እንዴት እንደሚሰሩት ምሳሌዎችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመስራት (በመስጠት) ማሳየት፤
- በአንድ ክፍት ቦታ አንድ ቃል ብቻ እንዲሞሉ መግለፅ ፤
- በእያንዳንዱ ክፍት ቦታ ላይ የሚሞላው ቃል ከምንባቡ የተጓደለ ቃል ካልሆነ በስተቀር ተመሳሳይ ቃል መሙላት ዋጋ እንደማያሰጥ ማሳወቅ፤
- ፈተናውን ለመስራት በቂ ሰዓት እንዳላቸው ማሳውቅ፤
- ፈተናውን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከአካባቢው አለመራቅ፤

ከላይ ከተዘረዘሩት ሀሳቦች የምንረዳው የግንዛቤ ሙከራ (ፈተና)ከመሰጠቱ በፊት መምህሩ ለተማሪዎች ማሳወቅ የሚገባው ነጥቦች እና መምህሩም የሚተገብራቸው ናቸው፡፡ስለሆነም የፈተናውን ዓላማ ማሳወቅ፣መፅሐፉን በፈተና ጊዜ መጠቀም ሳይሆን ቀደም ብለው እንዲያነቡት መንገር፣ፈተናው እንዴት እንደሚሠሩት ምሳሌዎችን መስጠት ፣ተመሳሳይ ቃሎችን መጠቀም እንደሌለባቸው ማሳወቅ ሲሆን፤መምህሩም ፈተናው በሚሰጥበት ጊዜ ከአካባቢው መራቅ እንደሌለበት ነው፡፡

ተማሪዎቹ ከላይ የተዘረዘሩትን አካሔዶች ተከትለው የወሰዱትን ሙከራ (ፈተና)ወደ እርማት ከመግባት በፊት የተለያዩ የማጣራት ሥራ ማከናወን ለምሳሌ የተዘለሉ ጥያቄዎችንና ከአንድ ቃል በላይ በክፍት ቦታው ላይ የተሞሉ እና ወዘተ ናቸው፡፡እርማቱ ከምንባቡ የተጓደለውን ቃል መሰረት በማድረግ ማረም፡፡ከዚያም በሚያገኙት ነጥብ መለየት የሚቀጥለው ተግባር ነው፡፡ከዚህ አንፃር የነጥብ አሰጣጥ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ መንገዶችን ቢከተሉም የሚመቸው የነጥብ አሰጣጥ ተማሪዎች የሰጡትን ትክክለኛ መልስ አጠቃላይ በመቁጠር በ2 ማባዛት እና በሚከተለው ሁኔታ መተርጎም ነው፡፡

- 60% እና በላይ የሆነ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ምንባቡን ያለምንም ችግር በብቃት እንደሚያነቡ ያሳያል፤
- ከ40 -59% የሆነ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ደግሞ መካከለኛ ደረጃ የሚያነቡ ስለሆነ ለተሻለ ውጤት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል፤
- ከ40% በታች የሆነ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው መረዳትአንደማይችሉ እና ጭንቀት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ያሳያል(DuBay2004፣27፤Vacca andRichard 1998፣159)::

ተነባቢነትና ስለተነባቢነት ቀመሮች የተለያዩ ምሁራን ያሰፈሩትን ለማየት ተሞክሯል፡፡ በመቀጠል ለምንባቦች ተነባቢነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሃሳቦችን እንቃኛለን፡፡

## 2.3 ለተነባቢነት መኖር አስተዋፅኦ ሚያደርጉ ሀሳቦች

### 2.3.1 ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር

ምንባብን ለማዘጋጀት የምንመርጠው ፅሑፍ ይዘቱ በተማሪው ላይ ከፍተኛ ፍላጎት መፍጠር ያለበት ሲሆን ፣ሰፋ ያለው ክፍል እና ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ስለሆነም የተማሪዎችን ፍላጎት መያዝ ወይም ተማሪዎች ፍላጎት ሊኖራቸው የሚችልበትን ምንባብ ለመምረጥ ለተማሪዎች መጠይቅ በመበተን ማሰስ ይቻላል ፡፡በርግጥ በዚህ የተማሪውን ፍላጎት በማሰስ ሒደት ሁሉም ተማሪ አንድ ዓይነት ፍላጎት ይኖረዋል ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ለአንዱ የሚያስደስተው ሌላውንላያስደስተውይችላል፡፡ይሁንእንጂ እነዚህን የተማሪዎች የፍላጎት ልዩነቶች ለማካተት እንዲያግዝ ይረዳ ዘንድ ምንባቦቹ የተለያዩ ርዕሶችንና ጉዳዮችን ማካተት እንዲሁም ፅሑፉ በቀላሉ የሚነበብ ተማሪው ሊያነብ የሚያጓጓው እና ሁሉንም የሚያማክል ፅሑፍ መለየትና ማዘጋጀት ያስፈልጋል(Harmer 2002፤Wallace 1993)::

በማያያዝምNuttal(1982፣30)፤ Wallace(1993፣71-75) ለምንባብነት የሚመረጡ ፅሑፎች የሚከተሉትን ሀሳቦች ከግምት ውስጥእንዲያስገቡ እንደመስፈርት አስቀምጠዋል።

ሀ/ፅሑፉ (ምንባቡ) ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ወይም ይበልጡን መተግበር መቻል አለመቻሉን መመርመር

- ምንባቡ ተማሪዎቹን አዲስና ጠቃሚ ከሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ና ሀሳቦች ጋር የሚያስተዋውቅ፣ ሌሎች የሚያስቡትንና የሚሰማቸውን ስሜት እንዲረዱ ፍንጭ የሚሰጥ እንዲሁም የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ለማጎልበት የተመቻቸ፤
- የፅሑፉ ይዘት የተማሪውን ዳራ ያገናዘበ እና ፍላጎት የሚያሳድር ሆኖ በራስ ተነሳሽነት እንዲያነቡ የሚጋብዝ ወይም ተነሳሽነት ኖሯቸው በመቀጠል ታሪኩን ፈልገው እንዲያነቡ የሚያበረታታ፤
- በየምዕራፉ የቋንቋ ቅርፅን ና ቃላትን ማስተማር የሚችል እና ቋንቋው ለክፍል ደረጃው ተገቢ የሆነ እንዲሁም የተማሪዎችን የማሰብ ችሎታ የሚያጎለብት፤
- ካርታ ፣ስዕላዊ መግለጫ ፣ግራፍና ሌሎች በፅሑፉ ውስጥ ያለውን ሀሳብ መሠረት አድርገው የተቀመጡ ለክፍል ውስጥ ክንውን የሚያመች፤
- ምንባቡ ለፆታ፣ለጎሳ፣ለህብረተሰብ አኗኗር ሁኔታ አዎንታዊ አመለካከት ያለው፤
- የመፅሐፉ ሽፋን ፣ቅርፁ፣የፅሑፉ አቀማመጥ፣ የተማሪውን ፍላጎት ቀስቃሽ የሆነ፤

ለ/ ተማሪዎች በምንባቡ ከተሳቡ በምንባቡ ክንውን የታቀፉ ፣የተሻለ የሚያነቡ ፣እና ትኩረት የሚሰጡ ይሆናሉ ፤እንዲህ ዓይነት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ሊረዳ የሚችለው ስለርዕሱ እንዲናገሩ ማድረግና ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ስለምንባቡ ይዘትና ምንነት እንዲተነብዩ በማድረግ ፍላጎታቸው እንዲነሳሳ ተፅእኖ ማሳደር ይቻላል።በዚህ ሒደት ውስጥ መተንበይ የሚችሉበትን አካሔድ በመጠቀምና ፍላጎት የሚያሳድሩ

ክንውኖችን በመምረጥ ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የነበራቸውን እውቀት ተጠቅመው ስለምንባቡ ግምታቸውን እንዲናገሩ በማድረግ ፍላጎታቸውን መያዝ ይጠቅማል( Harmer 2002)።

Grabe (2009፣179) እንደሚያስረዱት ተማሪው በምንባቡ ላይ ከፍተኛ ፍላጎት የሚኖረው ከሆነ ምንባቡን በማንበብም ሆነ በንባብ ሒደት ውስጥ ይበልጥ ተሳታፊ ይሆናል።ምክንያቱም ፍላጎት እያደገ ሲሄድ ውስጣዊ ተነሳሽነትን ይፈጥራል።ይህ አዎንታዊ ተነሳሽነት የአንባቢውን የአንብቦ የመረዳት ችሎታና በቀጣይነትም ምንባብ ለማንበብ እንዲገፋፋ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

በአጠቃላይ ለምንባብነት የሚመረጥ ፅሑፍ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚጠብቅ መሆን እንዳለበት መረሳት የለበትም።ይህም ተማሪዎች "የድርጊት ተሳታፊ ማድረግ የሚቻለው የምንመርጣቸው ሥራዎች ተማሪዎችን ያማከሉ ፍላጎትና ደረጃቸውን ሲጠብቁ ብቻ ነው" (Collie and Slater 1987፣7)።

## 2.3.2 ቃላት

የቃላት እውቀት መኖር አንብቦ ለመረዳት ወሳኝ ነው። ስለዚህ በምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ምን ማለት እንደሆነ ያልተረዳ ተማሪ ፅሑፉ ምን እንደሚል መረዳት አይችልም።ይህም በአዳዲስ ቃላት ብቻ የታጨቀ ምንባብ በተማሪው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድርመሆኑንያሳያል።በHarmer(2002፣80) አገላለፅ "አንባቢው በፅሑፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት በአብዛኛው የማያውቃቸው ከሆነ አጠቃላይ ሃሳብ ለማግኘትና ለመረዳት ይቸገራል። ስለዚህ ውጤታማ ለመሆን በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ይበልጥኑ የሚያውቀው መሆን አለበት።" እንዲሁም Hsuech and Nation (2000፣25) እንዳስፈሩት "ምንባቡን በበቂ ሁኔታ ለመረዳት ተማሪው የምንባቡን 98% ያህል ቃላትን የሚያውቃቸው መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።"

ከምሁራኑ ሀሳብ የምንረዳው የቃላት እውቀት መኖር አንብቦ ለመረዳት ወሳኝ ነው። በምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ምን ማለት እንደሆነ ያልተረዳ ተማሪ

ፅሑፉ ምን እንደሚል መረዳት አይችልም። ይህም በአዳዲስ ቃላት የታጨቀ ምንባብ በተማሪው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን ያሳያል ።

### 2.3.3 ዳራዊ እውቀት

በመማር ማስተማር ሒደት ውስጥ የተማሪውን ማንነት፣ ፍላጎት፣ የትምህርት ልምድ፣ አልፎ የመጣበት ሁኔታ እና ችሎታውን ማወቅ መሠረታዊ ጉዳይ ነው።ምክንያቱም ምንባቡ ስለምን ያነሳል ተማሪው ከዚህ በፊት ከሚያውቃቸው ሃሳቦች ጋር ግንኙነት አለው? ርዕሱን በማየት ሊገምት ይችላል?የሚሉና መሰል አይነት ጥያቄዎች መታሰብ ይገባቸዋል። ይህ ካልሆነና ምንባቡ ከተማሪው ዳራ ጋር ግንኙነት ከሌለው ተማሪው ምንባቡንለማንበብ ተነሳሽነት አይኖረውም። ስለዚህ ተማሪው የሚኖረው ዳራዊ እውቀት ለምንባብ ተነባቢነት፣ ትምህርቱን ለመረዳት፣ ውጤታማ ለመሆን አስተዋፅኦ አለው (Alderson 2001፤ Grabe 2009)።

### 2.3.4 የፅሑፍ አደረጃጀት

"በምንባብ ውስጥ አንቀፆች ቅደም ተከተላቸውን ይዘው ከተቀመጡ ለማንበብ ቀላልና ፍጥነትንም ይጨምራል። የተዋጣ የአንቀፆች አደረጃጀት ፍሰቱን የጠበቀ ስለሚሆን የምንባቡን ሃሳብ ለማስተላለፍ እና ለመረዳትም እገዛ ያደርጋል"(Alderson 2001፣60)። በተጨማሪ ካሴ (1998 ዓ.ም.፣39 ) William (1983)ን ጠቅሰው እንደገለፁት "የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከውጫዊ አካሉ እስከ ውስጣዊ ይዘቱ አደረጃጀት የተማሪውን ትኩረት የሚስብ የሚያነቃቃ በተለያዩ ዘዴዎች የቀረበ ሆኖ መደራጀት አለበት።"

### 2.3.5 የምንባብ ርዝመት

የምንባብ ርዝመት በተማሪዎች የንባብ ክሒል ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል።እንደ Day and park (2005፣20) አገላለፅ ተማሪው በምንባብነት የቀረበለትን አንብቦ ካልጨረሰ እራሱን ደካማ አንባቢ አድርጎ ስለሚቆጥር በትምህርቱ ውጤታማ አይሆንም። ይሁን እንጂ የንባብ ትምህርቱ የምንባቡን ርዝመት ይወስናል። ለምሳሌ የንባብ ትምህርቱ አላማ የአሰሳ ንባብ ከሆነ ለማስተማር ጥሩ መንገድ

የሚሆነው ረዥም ምንባቦችን ማቅረብና ለማንበብ የሚጀምርበትንና የሚጨርስበትን ሰዓት በመወሰን ነው፡፡ በሌላ በኩል የምንባቡ አላማ ዋና ሃሳብ መፈለግ ከሆነ አጠር ያለ ምንባብ ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ ለመማሪያነት የሚቀርቡ ምንባቦች ርዝመት አንድ ክፍለ ጊዜን መጣኝ መሆንእንደሚገባቸው ፤ሆኖም እንደምንባቡ ዓላማ የምንባቡ ርዝመት መለያየት እንዳለበት ያስረዱናል፡፡

## 2.4 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ሥር ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ የተለያዩ የጥናታዊ ሥራዎች ዳሰሳ ተደርጓል፡፡በቋንቋ ክፍለ ትምህርት በዚህ ርዕስ ላይ የተደረጉ የቀድሞ ጥናቶች ጥቂት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ጌታቸው (1986 ዓ.ም.) ለ10ኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች ብቃት በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ዓላማው አዲስአበባ በሚገኙ ስድስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል መምህራን ና ተማሪዎች ላይ የካሔዱት ጥናት ነው፡፡ጥናቱን ለማካሔድ የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ ቀመሮችን፣ የግንዛቤ ሙከራ ፈተናዎችን፣ መርሀ ትምህርቱንና የመማሪያ መፅሐፉን ተዛምዶ በመፈተሽ እና ለመምህራንና ለተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡ ውጤቱም ምንባቦቹ ተነባቢነት የሌላቸውተማሪዎቹም የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ መርሀ ትምህርቱና ዝርዝር አላማዎቹም ለሁሉም ክሒሎችና የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ተመጣጣኝ ሥርጭት የሌላቸው መሆናቸውንና ፤በፅሑፍ መጠይቁ በተገኘው ምላሽ መሠረት ዳግሞ ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ዕድሜ ፣ልምድና አካባቢ ጋር ያላቸው ቅርበት በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በማመልከት በመጨረሻም በተቻለ መጠን ምንባቦቹን ከተማሪዎች ደረጃ ጋር ማመጣጠን እንደሚያስፈልግ በመጠቆም ጥናታቸውን ደምድመዋል፡፡

ሁለተኛው Berhe (1989 )በወቅቱ በሥራ ላይ የሚገኘው የ10ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት ደረጃና በመፅሐፉ የሚጠቀሙ ተማሪዎች የመረዳት ችሎታ በሚል ርዕስ የቀረበና

ዓላማው የእንግሊዝኛ፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮ ሳይንስና የሳይንስ መፃህፍት ተነባቢነት ደረጃ መለየት ሲሆን፤ አዲስ አበባ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ ያካሄዱት ጥናት ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀሙት Edward Fry ግራፍና የግንዛቤ ሙከራ ነው፡፡ የጥናታቸው ውጤት እንደሚያሳየው መማሪያ መፅሐፎቹ ለክፍል ደረጃው ተመጣጣኝ እንዳልሆኑ፣ተማሪዎቹ አንብበው እንደማይረዱ ያረጋገጡ ሲሆን፤ ለወደፊቱ አስፈላጊው ጥረት ተደርጎባቸው ፍላጎታቸውን የጠበቀና ለማንበብ ተነሳሽነት የሚፈጥር፣ እንዲሁም በእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙምንባቦች በክፍል እና በብሔራዊ ፈተና ቢካተቱ በሚል ጥናቱን አጠቃለዋል፡፡

ሦስተኛው Mehari (2004) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ላይ የካሔዱት ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በአራተኛ ክፍል ትግርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች የተነባቢነት ደረጃ መመርመር በሚል ርዕስ በአንድ ትምህርት ቤት ላይ የተካሔደ ነው፡፡ጥናቱን ለማካሔድ የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ፣የግንዛቤ ሙከራ፣ ለተማሪዎች ቃለጠይቅ በማቅረብና የምንባቦቹን ተነባቢነት አስመልክቶ የመምህራንን አስተያየት ለመመርመር ደግሞ ለመምህራን ቼክሊስት በማዘጋጀት ነው፡፡ ውጤቱም ከቀመር በተገኘው ውጤት መሠረት ምንባቦቹ ተነባቢነት የሌላቸው መሆኑን፣ከግንዛቤ ሙከራ የተገኘው ውጤት ደግሞ ተማሪዎቹ አንብበው መረዳት እንደማይችሉ፣ ከቃለመጠይቁና ከቼክሊስቱ ውጤትም አዎንታዊ ምላሽ እንደሌላቸው በመግለፅ በመፅሐፉ ላይ የእርማት ሥራ ተካሒዶ መቅረብ እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ይህ የኔው ጥናት ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች ጋር የመመሳሰል ባህርይ የሚታይበት ቢሆንም የሚለይባቸው ነገሮች አሉት፡፡ ይህ ጥናት የተካሔደበት የመማሪያ መፅሐፍ፣ አገልግሎት ዘመን፣ የክፍል ደረጃ ና ቋንቋ እንዲሁም ጥናቱ የተካሔደበት ክልል ይለያል፡፡

በአጠቃላይ በቋንቋ ክፍለ ትምህርት የምንባቦች ተነባቢነት በተመለከተ የተሠሩ ሥራዎች ትኩረት ሰጥቶ በመፈተሽ አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን ለማየት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ንድፍና ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2004 ዓ.ም. በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት መፈተሽ ነው።ጥናቱ የተነሳበትን የምርምር ጥያቄ ለመመለስና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ይችል ዘንድ ዓይነታዊ ና መጠናዊ ዘዴን ተጠቅሟል፤ዓይነታዊ የአጠናን ዘዴ በመጠቀም ገላጭ በሆነ መንገድ የተተነተኑት በክፍል ደረጃው በማስተማር ላይ ከሚገኙ መምህራን በቃለመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ናቸው። እንዲሁም በፈተና፣ በፅሑፍ መጠይቅ ና በቀመር ተሰልተው የተገኙ ውጤቶቻቸው መጠናዊ ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል።

### 3.2. የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ለጥናቱ በዋነኛነት የመረጃ ምንጭ የሆነው2004ዓ.ም.በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችሲሆኑ፤በአጋዥነት ጥናቱ በሚካሔድበት የደቡብ ክልል ዋና ከተማ ሀዋሳ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 10ኛክፍል አማርኛ ቋንቋ  በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራንናየሚማሩ ተማሪዎች ናቸው።ምክንያቱም የጥናቱ ትኩረት ከላይ በተጠቀሰው ክፍል የሚገኘው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመሆኑ ነው።

### 3.3 የናሙና አመራረጥ

#### 3.3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሔደው በደቡብ ክልል ዋና ከተማ ሀዋሳ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ትምህርትቤቶቹ በከተማው ውስጥ በመገኘታቸው እና አጥኚዋ ጥናቱን በምታካሂድበት ጊዜ የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ተጠኚ መምህራን መልካም ፈቃደኝነት ይኖራል ተብሎ የታሰበ በመሆኑ እንዲሁም ቅርበትንም ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።  ስለሆነም ከትምህርት መምሪያ አስተዳደር በተገኘው

መረጃ መሠረት አሥራ ሦስት (13) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ሁ/ደ/ት/ቤቶች) አሉ፡፡ከእነዚህ ውስጥ አራቱእስከ መሰናዶ የደረሱ ፣አምስት እስከ 10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ እና አራቱበ2008 ዓ.ም.9ኛ ክፍል የከፈቱ ናቸው፡፡በመሆኑም የጥናቱን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ እስከ መሰናዶ የደረሱ ትምህርት ቤቶች ና 10ኛ ክፍል የሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የተቀሩት አራቱ ትምህርት ቤቶች በ2008ዓ.ም. 9ኛ ክፍል የከፈቱ በመሆናቸው ጥናቱ የማይመለከታቸው ናቸው፡፡የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑሦስት ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በተራ ዕጣናሙና አመራረጥ ስልት ነው፡፡ይህ የናሙና አወሳሰድ ስልት የተመረጠበት ምክንያት እኩል የመመረጥ እድል ስለሚሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም የዘጠኙን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስሞች ተመጣጣኝ መጠን ባላቸው ወረቀቶች ላይ ከተፃፈ በኃላ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቀለሉ፡፡ከተቀላቀሉት ወረቀቶች ሦስት ዕጣ ብቻ እንዲወጣ ተደረገ፡፡ በሶስቱ ዕጣዎች የተመረጡት ትምህርትቤቶች አዲስከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ፣አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ እና ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ-3 በናሙናነት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች፣ተማሪዎችና ምድቦች

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤት ስም | የተማሪዎች ብዛት | የምድቦች ብዛት | የተመረጡ ምድቦች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት(አ/ከ/ሁ/ደ/ናመ/ት/ቤት) | 867 | 18 | 3 |
| 2 | አዳሬሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት(አ/ሚ/ሁ/ደ/ት/ቤት) | 302 | 6 | 3 |
| 3 | ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት(ም/ጮ/ሁ/ደ/ት/ቤት) | 300 | 6 | 3 |
| ድምር | | 1469 | 30 | 9 |

ምንጭ ፡- ከሀዋሳ ትምህርት መምሪያ ትምህርት ዘርፍ የተገኘ መረጃ

### 3.3.2 የምድቦች ናሙና አመራረጥ

የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ከተጠናቀቀ በኃላ የሚቀጥለው ተግባር ምድቦችን መምረጥ ነበር ፤ስለዚህም በጥናቱ የሚታቀፉትን ምድቦች ለመምረጥ በመጀመሪያ ከየትምህርት ቤቱ ትምህርት ዘርፍ ምን ያህል ምድቦች እንደሚገኙ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ከዚያም በተራ ዕጣ የናሙና አመራረጥ ስልት በመጠቀም ከየትምህርት ቤቱ ሦስት ሦስት ምድቦች በአጠቃላይ ዘጠኝ (9) ምድቦች ተመርጠዋል፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

የምድቦች እጣ የማውጣት ሂደት ከተከናወነ በኃላ ከየምድቡ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች ቁጥር ለመወሰን በአንድ ምድብ ምን ያህል ተማሪዎች እንደሚገኙ መረዳት ነበር፡፡በናሙናነት ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች ከየትምህርት ዘርፉ በተገኘው መረጃ መሠረት በየምድቡ የሚገኙ የተማሪዎች ቁጥር ከ50-55መሆኑ ተረጋግጧል፡፡በአንድ ምድብ በአማካይ የተማሪዎች ቁጥር 50 እንደሆነ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡ስለሆነም ከሁሉም ተጠኚ ትምህርት ቤቶች ከየምድቡ አንድ አምስተኛ ተወስዷል፡፡ ለምሳሌ ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንድ ምድብ 50 ተማሪዎች ከተገኙ አንድ አምስተኛው ሲወሰድ የሚገኘው የተማሪዎች ቁጥር 50*1/5 =10 ይሆናል፡፡ የረድፍ ርቀቱን (ልዩነቱን) ለመወሰን በየምድቡ የሚገኘው አማካይ የተማሪዎች ቁጥር ለሚመረጡ ተማሪዎች ብዛት በማካፈል (50/10)=5 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በየ5 ተማሪዎች ልዩነት የተፈለገው ናሙና ቁጥር እስከሚገኝ ከየምድቡ ስም መቆጣጠሪያ ላይ መረጣው ተከናውኗል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪ (መነሻ)ቁጥር ለማወቅ ከ1-10 ከሚገኙት ውስጥ ዕጣ በማውጣት እና መነሻ ከ3ቁጥር በመጀመር አምስት አምስት በመዝለል ሲቆጠር በናሙናነት የተወሰዱ ተማሪዎች ቁጥር 3፣8፣13፣18፣23፣28፣33፣38፣43 እና 48 ይሆናሉ፡፡በአጠቃላይ 90 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሲሆኑ ፤ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የተመረጡት በተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡

### 3.3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የመምህራን ናሙና አመራረጥ በተመለከተ ጥናቱ በተካሔደባቸው ሦስት ትምህርት ቤቶች፤በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ የታቀፉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የክፍለ ጊዜ ስርጭቱ አነስተኛ በመሆኑ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በክፍል ደረጃው በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራንም ቁጥራቸው አናሳ ስለሆነ ጠቅላይ ናሙና አመራረጥ በመጠቀም ያሉት ተወስደዋል፡፡ ይሁን እንጂ አዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራኑ ቁጠራቸው ሦስት በመሆኑ በተራ ዕጣ ናሙና አመራረጥ ስልት በመጠቀም አንድ መምህር ብቻ ተወስዷል፡፡በአጠቃላይ ለቃለ መጠይቁ ሦስት መምህራን የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲያገለግሉ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ከነዚህም በዋናነት በሰነድ ምርመራ ምንባቦችን በመምረጥ የቀመርን ስሌት ተግባራዊ ማድረግ እና የግንዛቤ ሙከራ ማዘጋጀት ሲሆኑ፤በአጋዥነት ቃለመጠይቅና የፅሑፍ መጠይቅ አገልግሎት ላይ ውለዋል ፡፡ እነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 3.4.1 የሰነድ ምርመራ

ምንባቦቹ ለተመደቡበት ክፍል ደረጃ ተነባቢነታቸው የሚለካው በቀመሮች መሆኑ በምዕራፍሁለት ተገልጿል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጭ የሆነው በ2004ዓ.ም.በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ናቸው፡፡ተነባቢነታቸውን ለመፈተሽ ከመፅሐፉ መጀመሪያ መካከልና መጨረሻ ምንባቦችን መውሰድ እንደሚገባ (Nuttall 1982፣ 27፤ Clark and Staarr 1986፣ 201-202፤ Zamanian 2012 ፣44፤ Vacca and Richard 1998፣ 156-157) ይገልፃሉ ፡፡ ምንባቦች ከተመረጡ በኃላ ወደ ስሌት ለመግባት ቀዳሚው ተግባር ቀለም ቆጠራ በመሆኑ በመጀመሪያ በአጥኚዋ በመቀጠል ለአቻ መምህራን በማሳየት በመጨረሻም በሥነልሳን ባለሙያ

ከተረጋገጠ በኃላ ቀመሮቹ ሥራ ላይ ውለዋል።በመሆኑም ምዕራፍ ሁለት ላይ የሚገኙትን ቀመሮች ማለትም Flesch(1949) ቀመር እና Edward Fry(1977) ግራፍ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።ምክንያቱም እነዚህ ቀመሮች ቀላልና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያመቹ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡

## 3.4.2 ለተማሪዎች የተዘጋጀ የግንዛቤ ዝግ ሙከራ

ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው ምን ያህል እንደተረዱት አንዱ መለያው መንገድ የግንዛቤ ሙከራ ማዘጋጀት እና የተጓደሉትን ደራሲው የተጠቀመባቸውን ቃሎች እንዲሞሉ ማድረግ ነው። ስለሆነም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከመማሪያ መፅሐፉመጀመሪያ፣መካከልናመጨረሻ ላይ ምንባቦች ተወስደዋል። ከእያንዳንዱ ምንባብ 50 ክፍት ቦታ ያላቸው ፈተናዎች በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል።ፈተናዎቹ ለተጠኚዎቹ ከመቅረቡ በፊት በሁለት መምህራን እና በአማካሪዬ ታይቶ ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል።ፈተናዎቹ ግልፅ መመሪያ የሚገኝባቸውና ለእያንዳንዱ ፈተና በተማሪው ቁጥር መልስ መስጫ ወረቀት በማዘጋጀት ከፈተናው ጋር ተያይዞ ቀርቧል።የፈተናው አሰጣጥ በተያዘው እቅድ መሠረት ከትምህርት ሰዓታቸው ውጪ ቀድሞ በመገኘት ወይም ተመልሶ በመምጣት ማለትም ጠዋት 4፡00 ሰዓት ላይ እና ከሰዓት በኃላ10፡00 ሰዓት በመገኘት ተጠኚ ተማሪዎቹ ፈተናውን ተፈትነዋል።የፈተናው ሒደት የተቃና የሆነው በየትምህርት ቤቱ የትምህርት ዘርፍ ተጠሪዎች እና የሥራ ጓደኞቼ ድጋፍ አማካኝነት ነው።

የፈተናው እርማት አስተማማኝ እንዲሆን የሦስቱንም ፈተናዎች ትክክለኛ መልሶች ለሁለቱ አራሚዎች በመስጠት ታርሟል።በመጀመሪያ አንደኛ አራሚ 12ኛ ክፍል ተማሪ ሁለተኛ አራሚ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ዓመት ሁለተኛ ድግሪ ተማሪ ስትሆን በመጨረሻም አጥኚዋ እርማቱን እደገና በማረጋገጥ እና ተፈታኞች ያገኙትን ትክክለኛ መልስ በሁለት በማባዛት ውጤቱ ከ100% ከተሞላ በኃላ የሦስቱንም አራሚዎች ውጤት በመደመርና አማካይ በማውጣት ምዕራፍ ሁለት በ2.2.4 ሥር በተቀመጠው ሀሳብ መሠረት ተተንትኗል።በአራሚዎች መካከል ስምምነት መኖሩን በመደበኛ ልይይት (ANOVA) የተረጋገጠ ሲሆን

ውጤቱ እንደሚያሳየው በፈተና አንድ (F=0.122,0.885>0.05) በፈተና ሁለት (F=0.073,0.930>0.05) እና በፈተና ሦስት (F=0.033,0.968>0.05) ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ውጤት 0.05 በላይ መሆኑ በአራሚዎች መካከል ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል። ዝርዝሩን አባሪ ዘጠኝ ላይ ይመልከቱ።

### 3.4.3 የፅሑፍ መጠይቅ

ለጥናቱ መረጃ ለማግኘት የፅሑፍ መጠይቁ በክለሳ ድርሳናቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ በአጥኚዋ የተዘጋጁ ናቸው።መጠይቁ ሦስት ክፍሎች አሉት፤ክፍል አንድ ስለተጠኚ ተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቅ ነው። ክፍል ሁለት ና ሦስት በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ሲሆኑ ሊክርት ስኬል መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው። በመሆኑም በሠንጠረዥ የቀረቡና በጣምእስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ መወሰንአልችልም ፣አልስማማም እና በጭራሽአልስማም የሚሉ አምስት መለኪያዎች ይገኙበታል።ተማሪዎቹ የሚስማሙበትን መርጠው ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት በሚገኘው ክፍትቦታ(✓) እንዲያስቀምጡ ተገልፆላቸዋል። የመጠይቁ ሦስተኛ ክፍል ምንባቦቹን በተመለከተ አስተያየታቸውን የሚገልፁበት ጥያቄ በመሆኑ ክፍት ቦታ ይገኛል።የጥያቄዎቹን ሀሳብና አቀራረብ ሁለተኛ ዓመት ሁለተኛ ድግሪ ተማሪ በሆነች መምህርት አስተያየት ከተሰጠ በኃላ ለሙከራ በጥናቱ ባልታቀፉ ምድቦች በአዳሬሚሌኒየም ትምህርት ቤት 15 ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተዋል።መመሪያዎችን ተግባራዊ አለማድረግና ሠንጠረዥን በአግባቡ አለመጠቀም የታዩ ችግሮች ነበሩ።በዚህ ምክንያት የመጠይቁ መመሪያ እንደገና ተብራርቶ ተፅፏል። በመጨረሻም ለጥናቱ አማካሪ በመላክ በድጋሚ ተስተካክሎ እና አስተማማኝነቱ በክሮንባኽ አልፋ ዘዴ ከተረጋገጠ በኃላ ተጠኚ ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል።ዝርዝሩን አባሪ 8 ላይ ይመልከቱ።

የፅሑፍ መጠይቁ ያስፈለገበት ምክንያት ከተጠኚ ተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፉን ምንባቦች በተመለከተ የተለያዩ ርዕሶች ማካተቱን ፣ሲያነቡ ቃላቱን መረዳት መቻላቸውን ፣የቀደመ ዕውቀታቸውን መሠረት አድርጎ መዘጋጀቱን እና የተማሪዎችን ፍላጎት የጠበቁ መሆናቸውን ተጨማሪ ሀሳብ በማግኘት ለማጠናከር ነው።

### 3.4.4 ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቆቹ የተዘጋጁት ጥናቱ በተካሔደባቸው ትምህርት ቤቶች ለ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ነው፡፡ መጠይቆቹ ምዕራፍ ሁለት ላይ የቀረቡትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በአጥኚዋ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የቃለመጠይቁ የመጀመሪያው ክፍል መጠይቁ ላይ የተሳተፉ መምህራንን አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መማሪያ መፅሐፉን ምንባቦች መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡የጥያቄዎቹ ይዘት በድህረ ምረቃ ተማሪዎች አስተያየት ተሰጥቶበት የሀሳብ አገላለፃቸው መንገድ እንዲስተካከል ተደርገዋል፡፡ በመጨረሻም ለጥናቱ አማካሪ በማቅረብ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎባቸው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡መምህራኑ በሚመቻቸው ቀን እና ሰዓት በትምህርት ቤት ውስጥ በመገኘት ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡ ቃለመጠይቁን ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት መምህራኑ ከመፅሐፉ ጋር ባላቸው ቀረቤታ ስለምንባቦቹ ይዘት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ስለተፈለገ ነው፡፡

### 3.5.የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት በተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በሰነድ ምርመራው ሦስት የተለያዩ ምንባቦችን በመውሰድ የምንባቦቹ ተነባቢነት በ Flesch ቀመር እና Edward Fry ግራፍ ከተፈተሸ በኃላ የተነባቢነት ደረጃቸው ምዕራፍ ሁለት ላይ የምሁራኑን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ቀርቧል፡፡ በመቀጠል ለዚህ ጥናት የመጀመሪያው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያየግንዛቤ ሙከራዎች በተመረጡ ናሙና ምንባቦች ማዘጋጀት ነው፡፡ ሙከራውንተጠኚተማሪዎች ከተፈተኑበኃላ የተለያዩ የማጣራት ሥራዎችተከናውነዋል፡፡ ሦስቱንም ሙከራዎች በተከታታይ የተፈተኑ ተማሪዎች ወረቀትተለይቶ በሦስት አራሚዎች ታርሟል፡፡የሦስት አራሚዎች አማካዩን ውጤትወስዶ በምዕራፍ ሁለት 2.2.4 ሥር የተጠቀሰውን የምሁራንን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ያለምንም ችግር በብቃት የሚያነቡ፣በመምህሩ ድጋፍ (መካከለኛ ደረጃ)እና አንብበው መረዳት የማይችሉ በማለት በሠንጠረዥ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በአጋዥነት የቀረቡት ቃለመጠይቅ

ናየፅሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ለመምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ ከእያንዳንዱ መምህር ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተገኘውን ምላሽ በመጭመቅ በገለፃ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም በተማሪዎች የተሞላው የፅሑፍ መጠይቅ ተማሪዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሠጡት ምላሾች ተደምረው በመቶኛ ስልት ከተቀመጡ በኃላ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በክፍት ቦታው ላይ የሰጡትን አስተያየቶች በማጠቃለል ተቀምጠዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ውጤት ትንተና

ከዚህ በፊት በቀረቡት ምዕራፎች እንደተገለፀው የጥናቱ ዋና አላማ በ2004 ዓ.ም በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት መፈተሽ ነው፡፡ስለሆነም የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ በሆኑት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በመጀመሪያው የትንተና ክፍል በሰነድ ፍተሻ አማካኝነት በመፅሐፉ ዉስጥ የሚገኙ ምንባቦችን በቀመር ስሌት የተገኙ ውጤቶች ቀርበዋል፡፡ በመቀጠል ከተጠኚ ተማሪዎች በፈተና የተገኙ ውጤቶች የተተነተኑ ሲሆን በፅሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በተናጠልና በማቀናጀት ተተንትነዋል፡፡

### 4.1. የምንባቦችንተነባቢነት ለመለካት ከቀመሮችና ከግንዛቤ ሙከራዎች የተገኙ መረጃዎች

#### 4.1.1 የFlesch ቀመር ስሌት

ከFlesch ቀመሮች ውስጥ የቅርብ ጊዜ የሆነውና ተሻሽሎ የቀረበውን ቀመር በመጠቀምበ100ቃሎች ውስጥ የሚገኙ ባለአንድ ቀለም ቃሎች ብዛት እና አማካይ የዐረፍተነገር ርዝመት (የቃሎች ብዛት ሲካፈል ለዐረፍተነገር ብዛት) በመውሰድና ቀመሩን ተግባራዊ በማድረግ ንባብ ቅለት ነጥብ ይገኛል፡፡ይህም የሦስቱም ናሙና ምንባቦች ውጤት በሠንጠረዥ አራት ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4በFlesch ቀመርየተገኙ የሶስቱ ናሙና ምንባቦች ውጤቶችና ምንባቦቹ የተገመቱለትየክፍል ደረጃ

| ናሙና | የምንባቦች ርዕስ | በ100 ቃሎች ውስጥ የቀለሞች ብዛት | በ100 ቃሎች ውስጥ የዐረፍተ ነገሮች ብዛት | በ100 ቃሎችውስጥ ባለ1 ቀለምቃሎች ብዛት(nosw) | አማካይ የዐረፍተ ነገር ርዝመት (sl) | የንባብ ቅለት ነጥብ | ናሙናዎች የተገመቱለት የክፍል ደረጃ | የሶስቱን ምንባቦች አማካይ የንባብ ቅለት ነጥብ | መፅሐፉ የተገመተለት የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቋንቋ አጀማመር | 329 | 8.3 | 11 | 12 | -26.1 | ኮሌጅ ላጠናቀቁና በላይ | -19.3 | ኮሌጅ ላጠናቀቁና በላይ |
| 2 | "ምንም የማይቻል ነገር የለም" | 267 | 14.1 | 18 | 7 | -9.8 | ኮሌጅ ላጠናቀቁና በላይ | | |
| 3 | "የጉለሌው ሠካራም" | 271 | 10.1 | 12 | 9.9 | -22.3 | ኮሌጅ ላጠናቀቁና በላይ | | |

የምንባቦችን ተነባቢነት ደረጃ ለማወቅ ከመጽሐፉ ምንባቦች መጀመሪያ፣መካከልና መጨረሻ ገጽ ላይ የሚገኙ ምንባቦችን በመውሰድና Flesch ቀመር ተግባራዊ በማድረግ የተገኘውን የእያንዳንዱን ናሙና ምንባብ የንባብ ቅለት ነጥብ ሠንጠረዥ ላይ ተገልጿል፡፡በFlesch ቀመር የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ናሙና አንድ የንባብ ቅለት ነጥብ -26.1፣የናሙና ሁለት የንባብ ቅለት ነጥብ -9.8 እና ናሙና ሦስት የንባብ ቅለት ነጥብ - 22.3 ሲሆን የሦስቱ ናሙና ምንባቦች አማካይ የንባብ ቅለት ነጥብ -19.3 ነው፡፡

ይህም ከምዕራፍ ሁለት 2.2.1 እነ Dubay(2004፣22)፤ Nasser (2014፣2046)፤ Zamanion (2012፣45) የFlesch ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥ ሰሌዳ መሠረት ምንባቦቹ የክፍል ደረጃውን እንደማይመጥኑ ያሳያል፡፡ ምክንያቱም በጣም ከባድ የተባለው የንባብ ቅለት ነጥብ 0-29 ሲሆን ከላይ የተገለፁት ከስሌት የተገኙት ውጤቶች ሠሌዳው ላይ ከሚገኙት ሀሣቦች ጋር ሲነፃፀሩ ምንባቦቹ ከታሰበው ክፍል ደረጃ በላይ እና ከባድ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

### 4.1.2 Edward Fry ግራፍ (1977)

የFry የተነባቢነት ግራፍ ቀላልና ፈጣን ሲሆን ፣ከአንደኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ለሚገኙ ምንባቦች ተነባቢነት መለኪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የFry ግራፍን ተግባራዊ ለማድረግ የዐረፍተነገሮች ብዛት እና የቀለሞች ብዛት ወሳኝ ናቸው፡፡ በመሆኑም በ Fry ግራፍ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ከናሙና ምንባቦች የተገኘውን ውጤት ከሠንጠረዥ 5 መመልከት ይቻላል ፡፡

ሠጠረዥ 5 ምንባቦቹ በ Fry ግራፍ የተገመቱለት ክፍል ደረጃ

| ናሙና | የምንባቦች ርዕስ | በ100 ቃሎች ውስጥ የቀለሞች ብዛት | በ100 ቃሎች ውስጥ የዐ.ነገሮች ብዛት | የቀለም ብዛት በአማካይ | ዐ.ነገር ብዛት በአማካይ | መፅሐፉ የተገመተለት ክፍል ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የቋንቋ አጀማመር | 329 | 8.3 | 289 | 10.8 | ኮሌጅ ላጠናቀቁ |
| 2. | "ምንም የማይቻል ነገር የለም" | 267 | 14.1 | | | |
| 3. | "የጉለሌው ሰካራም" | 271 | 10.1 | | | |

ከሠንጠረዥ 5 የምንረዳው የእያንዳንዱን ናሙና ምንባብ ቀለሞች በመውሰድ ከዚያም የሦስቱንም ናሙና ምንባቦች ቀለሞች መደመር እና ለሦስት በማካፈል አማካይ የቀለም ብዛት መፈለግ፤ እንዲሁም በእያንዳንዱ ናሙና ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን የዐረፍተነገሮች ብዛት በመውሰድ የሦስቱንም ናሙና ምንባቦች ዐረፍተነገሮች ብዛት ደምሮ ለሦስት ማካፈል ነው። በመጨረሻም አማካይ የቀለሞች ብዛት እና አማካይ የዐረፍተነገሮች ብዛት በግራፍ ላይ በማስፈር ምንባቦቹ የተገመቱለትን ክፍል ደረጃ ያመለክታል። ስለዚህ ከላይ እንደተጠቀሰው Fry ግራፍ ቀለሞች ብዛትና ለዐረፍተነገሮችብዛት ትኩረት ይሠጣል። ሠንጠረዡ እንደሚያሳየውም ምንባቦቹ በተናጠልም ይሁን በአማካይ ውጤት የተገመቱት ክፍል ደረጃ ኮሌጅ ሳጠናቀቁ ነው።ይህም ማለት ምንባቦቹ ከክፍል ደረጃው በላይ በመሆናቸው ተማሪዎች አንብበው ለመረዳት ይከብዳቸዋል።

### 4.1.3 ከግንዛቤ ዝግ ሙከራ የተገኘ ውጤት

በምዕራፍ ሁለት 2.2.2 የሚገኘው ሀሳብ ከመፅሐፉ መጀመሪያ፣መካከልና መጨረሻ ምንባቦቹ መመረጥ እንዳለባቸው ስለሚያሳስብ ለFlesch ቀመር ናFryግራፍ የተመረጡ ሦስት የናሙና ምንባቦች የግንዛቤ ሙከራ ጥያቄ ለማዘጋጀት አገልግለዋል። የሙከራውን አሰጣጥ ተግባራዊ ለማድረግ ጥናቱ በተካሄደባቸዉ ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ለተመረጡ ተማሪዎች የሌሎች አቻ መምህራን እርዳታ ታክሎበት ፈተናው በተለያዩ ጊዜያት ማትም በአዲስከተማ ሁለተኛ ደረጃናመሰናዶ ትምህርት ቤት 15/7/08፣21/7/08 እና 28/7/08 ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 6/7/08፣15/7/08 እና11/8/08 እንዲሁም አዳሬሚሌኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 8/7/08 ፣12/7/08 እና 19/7/08 በየትምህርት ቤቱ ተሰጥቷል። ፈተናውን የመፈተን ሂደት ከተከናወነ በኃላ በሦስት አራሚዎች ታርሞ የእያንዳንዱ ፈተናና የየትምህርትቤቱ ውጤት ተመዝግቧል ። የሦስቱም አራሚዎች አማካይ ውጤት ከአባሪ አምስት መመልከት ይቻላል።

ሠንጠረዥ6 የሦስቱም ትምህርትቤት የግንዛቤ ሙከራ አንድ የተማሪዎችውጤት

| የትምህርት ቤቶች ስም | ፆታ | የተጠኚዎች ብዛት | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 60ና ከ60 በላይ | | ከ40-59 | | ከ40 በታች | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| አዲስ ከተማ | ወ | 11 | - | - | 6 | 27.2 | 5 | 22.7 |
| | ሴ | 11 | 1 | 4.5 | 6 | 27.2 | 4 | 18.1 |
| | ድ | 22 | 1 | 4.5 | 12 | 54.5 | 9 | 40.9 |
| አዳሬ ሚሌኒየም | ወ | 14 | 4 | 18.1 | 5 | 22.7 | 5 | 22.7 |
| | ሴ | 8 | 2 | 9.0 | 3 | 13.6 | 3 | 13.6 |
| | ድ | 22 | 6 | 27.2 | 8 | 36.3 | 8 | 36.3 |
| ምስራቅ ጮራ | ወ | 11 | 1 | 5.2 | 4 | 21.0 | 6 | 31.5 |
| | ሴ | 8 | - | - | 4 | 21.0 | 4 | 21.0 |
| | ድ | 19 | 1 | 5.2 | 8 | 42.1 | 10 | 52.6 |
| ጠቅላላ ድምር | | 63 | 8 | 12.6 | 28 | 44.4 | 27 | 42.8 |

ሠንጠረዥ 6 የሚያሳየው የሦስቱም ትምህርትቤቶች ተጠኚ ተማሪዎች በግንዛቤ ሙከራ አንድ ያስመዘገቧቸው አማካይ ውጤቶች ናቸው፡፡ይኸውም አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት 60 ና ከ60 በላይ ያስመዘገበችው1(4.5%) ሴት ስትሆን ከወንዶች 60ናከ60 በላይ ያስመዘገቡ የሉም፡፡ ከ40-59 ያስመዘገቡ 6(27.2%) ወንዶችእና 6(27.2%) ሴቶች በድምሩ 12(54.5%)፣ ከ40 በታች ያስመዘገቡ 5(22.7%) ወንዶች እና 4(18.1%) ሴቶች በድምሩ 9(40.9%) ተማሪዎች ናቸው፡፡አዳሬ ሚሌኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 60 ና ከ60 በላይ 4(18.1%) ወንዶች እና 2(9 %) ሴቶች በድምሩ 6(27.2%)፣ከ40-59 ያስመዘገቡ 5(22.7%)ወንዶች እና 3(13.6%) ሴቶች በድምሩ 8(36.3%) ሲሆኑ ከ40 በታች 5(22.7%) ወንዶች እና 3(13.6%) ሴቶች በድምሩ 8(36.3%) ናቸው፡፡እንደዚሁ ከምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 60ና ከ60 በላይ ያመጣ 1(5.2%) ወንድ ሲሆን ሴቶች ያስመዘገቡ የሉም፡፡ ከ40-59 ያመጡ 4(21%) ወንዶች ና 4(21%)ሴቶች በድምሩ 8(42.1%) ሲሆኑ ከ40 በታች ያስመዘገቡ 6(31.5%) ወንዶች ና 4(21%) ሴቶች በድምሩ 10(52.6%) ተማሪዎች ናቸው፡፡

የግንዛቤ ሙከራ አንድ ድምር ውጤት የሚያሳየው 8(12.6%) 60 ና ከ60 በላይ ያመጡ መሆናቸው ያለምንም ችግር የሚያነቡ፤ 28(44.4%) ከ40-59 ያመጡ ለተሻለ ውጤት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው እና 27(42.8%) ከ40 በታች ያመጡ አንብበው መረዳት የማይችሉና ጭንቀት ደረጃ ላይ የሚገኙ እንደሆኑ ምዕራፍ ሁለት 2.2.4 ላይ የምሁራኑ ሀሳብ ያስገነዝባል፡፡በአጠቃላይየሙከራ አንድ ውጤትየሚያሳየው የተማሪዎች ውጤት መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የመምህር ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7የሦስቱ ትምህርትቤት የግንዛቤ ሙከራ ሁለት የተማሪዎች ውጤት

| የትምህርት ቤቶች ስም | ፆታ | የተጠኚዎች ብዛት | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 60ና ከ60 በላይ | | ከ40-59 | | ከ40 በታች | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| አዲስ ከተማ | ወ | 11 | - | - | 7 | 31.8 | 4 | 18.1 |
| | ሴ | 11 | - | - | 5 | 22.7 | 6 | 27.2 |
| | ድ | 22 | - | - | 12 | 54.5 | 10 | 45.4 |
| አዳሬ ሚሊኒየም | ወ | 14 | - | - | 6 | 27.2 | 8 | 36.3 |
| | ሴ | 8 | 1 | 4.5 | 3 | 13.6 | 4 | 18.1 |
| | ድ | 22 | 1 | 4.5 | 9 | 40.9 | 12 | 54.5 |
| ምስራቅ ጮራ | ወ | 11 | 1 | 5.2 | 5 | 26.3 | 5 | 26.3 |
| | ሴ | 8 | 1 | 5.2 | 4 | 21.0 | 3 | 15.7 |
| | ድ | 19 | 2 | 10.5 | 9 | 47.3 | 8 | 42.1 |
| ጠቅላላ ድምር | | 63 | 3 | 4.76 | 30 | 47.6 | 30 | 47.6 |

ሠንጠረዥ 7ሚያሳየው የግንዛቤ ሙከራ ሁለት ውጤት ነው፡፡ ከአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት 60 ና ከ60 በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች የሉም፡፡ ሆኖም ከ40-59 ያስመዘገቡ 7 (31.8) ወንዶች እና 5 (22.7%) ሴቶች በድምሩ 12(54.5%) ሲሆኑ ከ40 በታች ደግሞ 4(18.1%) ወንዶች እና 6(27.2%) ሴቶች በድምሩ 10(45.4%) ተማሪዎች

ናቸው። ከአዳሬ ሚሌኒየም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 60 ና ከ60 በላይ 1(4.5%) ሴት፣ ከ40-59 ደግሞ 6(27.2%) ወንዶች እና 3(13.6%) ሴቶች በድምሩ 9(40.9%) ሲሆኑ ከ40 በታች ያስመዘገቡ 8(36.3%) ወንዶች እና 4(18.1%) ሴቶች በድምሩ 12(54.5%) ተማሪዎች ናቸው። ከምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 60 ና ከ60 በላይ 1(5.2%) ወንድ እና 1(5.2%) ሴት በድምሩ 2(10.5%) ከ40-59 የሆነ ውጤት ያስመዘገቡ ደግሞ 5(26.3%) ወንዶች እና 4(21.%) ሴቶች በድምሩ 9(47.3%) ከ40 በታች ውጤት 5(26.3%) ወንዶች እና 3(15.7%)ሴቶች በድምሩ 8(42.1%) ተማሪዎች ናቸው።ድምር ውጤት የሚያሳየው 60 ና ከ60 በላይ ያስመዘገቡ 3(4.76%) ሲሆን ከ40-59 እና ከ40 በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር 30(47.6%) ነው። በአጠቃላይ ሙከራ ሁለት የተማሪዎች ውጤት የሚያሳየው ለተሻለ ውጤት የመምህር ድጋፍ እንደ ሚያስፈልጋቸው ያስረዳል።

ሠንጠረዥ 8የሦስቱ ትምህርትቤት የግንዛቤ ሙከራ ሦስት የተማሪዎች ውጤት

| የትምህርት ቤቶች ስም | ፆታ | የተጠኚዎች ብዛት | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 60ና ከ60 በላይ | | ከ40-59 | | ከ40 በታች | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| አዲስ ከተማ | ወ | 11 | - | - | 4 | 18.1 | 7 | 31.8 |
| | ሴ | 11 | - | - | 8 | 36.3 | 3 | 13.6 |
| | ድ | 22 | - | - | 12 | 54.5 | 10 | 45.4 |
| አዳሬ ሚሌኒየም | ወ | 14 | - | - | 3 | 13.6 | 11 | 50 |
| | ሴ | 8 | - | - | 1 | 4.5 | 7 | 31.8 |
| | ድ | 22 | - | - | 4 | 18.1 | 18 | 81.8 |
| ምሰራቅ ጮራ | ወ | 11 | - | - | 7 | 36.8 | 4 | 21.0 |
| | ሴ | 8 | - | - | 3 | 15.7 | 5 | 26.3 |
| | ድ | 19 | - | - | 10 | 52.6 | 9 | 47.3 |
| ጠቅላላ ድምር | | 63 | - | - | 26 | 41.2 | 37 | 58.7 |

ሠንጠረዥ 8 ላይ የሚታየው የግንዛቤ ሙከራ ሦስት የተማሪዎች ውጤት ሲሆን በዚህ ሙከራ በሦስቱም ትምህርትቤቶች 60 እና ከ60 በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች የሉም ። በሌላ በኩል ከ40-59 ያስመዘገቡ ተማሪዎች ከአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት 4(18.1%) ወንዶች እና 8(36.3%) ሴቶች በድምሩ 12(54.5%) ሲሆኑ ከ40 በታች ያስመዘገቡ ደግሞ 7(31.8%) ወንዶች እና 3(13.6%) ሴቶች በድምሩ 10(45.4%) ተማሪዎች ናቸው። ከአዳሬ ሚሌኒየም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ40-59 ውጤት ያላቸው 3(13.6%) ወንዶች እና 1(4.5%) ሴት በድምሩ 4(18.1%) እንዲሁም ከ40 በታች 11(50%) ወንዶች እና 7(31.8%) ሴቶች በድምሩ 18(81.8%) ተማሪዎች ናቸው። ከምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 7(36.8%) ወንዶች እና 3(15.7%) ሴቶች በድምሩ 10(52.6%) ከ40-59 ያስመዘገቡ ሲሆኑ 4(21%) ወንዶች እና 5(26.3%) ሴቶች በድምሩ 9(47.3%) ተማሪዎች ከ40 በታች የሆነ ውጤት ያገኙ ናቸው። ስለዚህ በግንዛቤ ሙከራ ሦስት ከ40-59 ያገኙ ተማሪዎች ብዛት 26(41.2%) ከ40 በታች ያገኙ ተማሪዎች ደግሞ 37(58.7%)ናቸው።በምዕራፍ ሁለት እንደምሁራኑአገላለፅተማሪዎቹ በቅደም ተከተል በድጋፍ የሚያነቡ እና በጭንቀት የሚያነቡ ናቸው። በአጠቃላይ በሙከራ ሦስትከ40 በታች ያገኙ ተማሪዎችቁጥር ከፍ ብሎ በመታየቱ በጭንቀት የሚያነቡ መሆናቸውን ያስረዳል።

ሠንጠረዥ 9የሦስቱ ግንዛቤ ሙከራዎች ጥቅል አማካይ የተማሪዎች ውጤት

| የትምህርት ቤቶች ስም | ፆታ | የተጠኚዎች ብዛት | የነጥብ አሰጣጥ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 60ና ከ60 በላይ | | ከ40-59 | | ከ40 በታች | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| አዲስ ከተማ | ወ | 11 | - | - | 6 | 27.2 | 5 | 22.7 |
| | ሴ | 11 | - | - | 5 | 22.7 | 6 | 27.2 |
| | ድ | 22 | - | - | 11 | 50 | 11 | 50 |
| አዳሬ ሚሌኒየም | ወ | 14 | - | - | 9 | 40.9 | 5 | 22.7 |
| | ሴ | 8 | - | - | 5 | 22.7 | 3 | 13.6 |
| | ድ | 22 | - | - | 14 | 63.6 | 8 | 36.3 |
| ምስራቅ ጮራ | ወ | 11 | - | - | 7 | 36.6 | 4 | 21.0 |
| | ሴ | 8 | - | - | 4 | 21.0 | 4 | 21.0 |
| | ድ | 19 | - | - | 11 | 57.8 | 8 | 42.1 |
| ጠቅላላ ድምር | | 63 | - | - | 36 | 57.1 | 27 | 42.8 |

ሠንጠረዥ 9 የሚያሳየው የሦስቱም ትምህርትቤቶች ተማሪዎች በሦስቱም የግንዛቤ ሙከራዎች ያስመዘገቧቸው አማካይ ውጤት ነው፡፡ የሠፈረው ውጤት በቅደም ተከተል ሲገለፅ አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት ከ40-59 ያስመዘገቡ 6(27.2%) ወንዶች እና 5(22.7%) ሴቶች በድምሩ 11(50%)፣አዳሬ ሚሌኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 9(40.9%) ወንዶች እና 5(22.7%) ሴቶች በድምሩ 14(63.6%)፣ ምሰራቅ ጮራ 7(36.8%) ወንዶች እና 4(21.0%) ሴቶች በድምሩ 11(57.8%) ተማሪዎች የመምህሩ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው መረጃው ያሳያል፡፡ ሌሎች ከ40 በታች ያስመዘገቡ ከአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት 5(22.7%) ወንዶች እና 6(27.2%) ሴቶች በድምሩ 11(50%)፣ አዳሬ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 5(22.7%) ወንዶች እና 3(13.6%) ሴቶች በድምሩ 8(36.3%) ፣ምሰራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 4(21%) ወንዶችና 4(21%) ሴቶች በድምሩ 8(42.1%) ተማሪዎች በጭንቀት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ሠንጠረዡ ላይ የሠፈረው ውጤት ያሣያል፡፡ በአጠቃላይ ሠንጠረዡ እንደሚያስረዳው የሦስቱም ትምህርትቤቶች የሦስቱም ሙከራዎች አማካይ የተማሪዎች ውጤት ድምር ከፍተኛው 36(57.1%) ነው፡፡ በመሆኑም ምዕራፍ ሁለት ላይ በ2.2.4 ሥር ምሁራን ባሰፈሩት ሀሳብ መሠረት ተማሪዎቹ በመካከለኛ ደረጃ የሚያነቡ ስለሆነ ለተሻለ ውጤት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል፡፡ 27(42.8%) ተማሪዎች ደግሞ ምንባቡን አንብበው መረዳት እንደማይችሉና ጭንቀት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መረጃው ይጠቁማል፡፡ሆኖምከጠቅላላው የግንዛቤ ሙከራ ውጤት መረጃ መሠረት ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ የሚያነቡ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

## 4.2. ከፅሑፍ መጠይቅ ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች

ቀደም ሲል እንደተብራራው በተማሪዎቹ የሚሞላው መጠይቅ ሶስት ክፍሎች አሉት፤የመጠይቁ ክፍል አንድ ዳራ ነክ ጥያቄዎች ሲሆኑ ክፍል ሁለት እና ሶስት በመማሪያ መፅሐፉ ምንባቦች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡በዚህ መሠረት በፅሑፍ መጠይቁ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

ሠንጠረዥ 10 ተጠኚ ተማሪዎች ጾታ፣ ዕድሜና የአፍ መፍቻ ቋንቋ

| ፆታ | | | | ዕድሜ | | | | የአፍ መፍቻ | | | | ቋንቋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | | ሴ | | 15-19 | | 20-24 | | አማርኛ | | ሲዳሚኛ | | ሌሎች | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 38 | 42.2 | 36 | 40 | 50 | 55.5 | 24 | 26.6 | 37 | 41.1 | 32 | 35.5 | 5 | 5.5 |

መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች የግንዛቤ ሙከራ የተፈተኑ ተማሪዎች ናቸው፡፡ መጠይቁን እንዲሞሉ ከታቀደው 48 ወንዶች እና 42 ሴቶች በድምሩ 90 (42%) ተማሪዎች ውስጥ በትክክል ሞልተው የመለሱ 38 (42%)ወንዶች እና 36 (40%) ሴቶች በድምሩ 74 (82%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተቀሩት 5 (5.5%) በክፍል ሁለት ጥያቄ ላይ ስህተቶች የሰሩ 3 (3.3%) ወረቀቶች ያልተመለሱ እና 8 (8.8%) ተማሪዎች ደግሞ ከትምህርት ቤት በመቅረት ምክንያት ያልሞሉ ናቸው፡፡ ይህም መጠይቁን በትክክል የሞሉ ተማሪዎች74(66.6%) በመሆናቸው በዚህ ቁጥር የሚሰበሰቡ መረጃዎች ጥናቱን ለማካሔድ አስተማማኝ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ መጠይቁን በትክክል ሞልተው ከመለሱ ተማሪዎች መካከል የ50(55.5%) ተማሪዎች ዕድሜ ከ15-19 ውስጥ ሲሆኑ የ24(26.6%) ተማሪዎች ደግሞ 20-24 ዕድሜክልል ውስጥ መሆናቸውን ከሠንጠረዡ እንረዳለን፡፡

37 (41.1%) ተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋቸውአማርኛ ሲሆን፤ 32 (35.5%) ተማሪዎች ደግሞ አፋቸውን የፈቱት በሲዳሚኛ ቋንቋ ነው፡፡ የቀሪዎቹ 5 (5.5%) ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከአማርኛ እና ከሲዳሚኛ ቋንቋ ውጪ እንደሆነ ሠንጠረዡ ላይ የሰፈረው መረጃ ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 11 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ንባብ ፍላጎት ከመፍጠር አንፃር ከተጠኚተማሪዎች የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መለኪያዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጭራሽ አልስማማም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ቅድመምንባብ ጥያቄዎችን በማወያየትየዕለቱን ምንባብእንዳነብ ያበረታታሉ፡፡ | 19 | 33.7 | 12 | 16.5 | 4 | 2.7 | 35 | 47.2 | 3 | 4.0 |
| 4 | ምንባቦቹ ወቅታዊ አዲስና ጠቃሚ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር እንድንተዋወቅ ይረዳሉ፡፡ | 28 | 37.8 | 5 | 6.7 | 2 | 2.7 | 30 | 40.5 | 9 | 12 |
| 5 | የምንባቦቹ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች የንባብ ፍላጎት እንዲኖረኝ ይጋብዛሉ፡፡ | 10 | 13.5 | 31 | 41.8 | 4 | 5.4 | 27 | 36.4 | 2 | 2.7 |
| 7 | በማማሪያመፅሐፉ ውስጥ የሚገኙምንባቦችንበማነብበ ትጊዜበይዘቶቹእደሰታለሁ | 10 | 13.5 | 20 | 27.0 | 13 | 17.5 | 26 | 35.1 | 5 | 6.7 |
| 10 | የመፅሐፉንሽፋን ፣ቅርፁ፣ህትመቱ፣ውስጡ የሚገኙሥዕሎች፣ሠንጠረ ዦች ያንተን የንባብ ፍላጎት ቀስቃሽ ናቸው፡፡ | 34 | 45.9 | 26 | 35.1 | 3 | 4.0 | 5 | 6.7 | 6 | 8.1 |

ከላይ የሚገኘው ሠንጠረዥ11 የሚያሳየው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ከተማሪዎች ንባብ ፍላጎት አንፃር ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች በማቅረብ ተሳትፎን ያበረታታሉ ለሚለው ምላሽ 19(33.7%) በጣም እስማማለሁ፣ 12(16.5%) እስማማለሁ አዎንታዊ ምላሽ ና ፤ 4(5.4%) መወሰን አልችልም፣ 35(47.2%) አልስማማም እና 3(4.0%)በጭራሽ አልስማማም የሚል አሉታዊ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4 የምንባቦቹን ወቅታዊነት በተመለከተ 28(37.8%) ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣5(6.7%)ተማሪዎች እስማማለሁ ፣2(2.7%) ተማሪዎችመወሰን አልችልም፣30(40.5%) ተማሪዎች አልስማማም እና 9(12%) ተማሪዎች በጭራሽ አልስማማም የሚሉ ምላሾች ሰጥተዋል ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5 የምንባቦቹ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች የንባብ ፍላጎት እንዲኖር ይጋብዛሉ ለሚለው የተገኘው ምላሽ 10(13.5%)ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 31(41.8%) እስማማለሁ፣ 4 (5.%) መወሰን አልችልም ሲሆን፤ 27(36.4%) አልስማማም እና 2(2.7%) በጭራሽ አልስማማም አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 7 በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን በማነብበት ጊዜ በይዘቶቹ እደሰታለሁ ለሚለው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 10(13.5%) በጣም እስማማለሁ እዲሁም 20(27%) ተማሪዎች እስማማለሁ ይህም አዎንታዊ ምላሾች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡13 (17.5%) ደግሞ መወሰን አልችልም ሲሆን፤ 26(35.1%)እና 5(6.7%) አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡ ስለዚህ መምህራኑ በቃለ መጠይቅ

ለቀረበላቸው ጥያቄ ተራ ቁጥር ሰባት ላይ የሰጡት ምላሽ ተማሪዎች እንዲያነቡ የሚያጓጉ ይዘቶች ጎልተው እንደማይታዩ ከገለፁት ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 10 የመማሪያ መፅሐፉ ሽፋን፣ ቅርፁ፣ህትመቱ ውስጡ የሚገኙ ስዕሎች ሠንጠረዦች የንባብ ፍላጎትን ቀስቃሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለቀረበውጥያቄ የተገኘው አዎንታዊ ምላሽ 34(45.9%)ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 26(35.1%)ተማሪዎች እስማማለሁ ሲሆን ፤3(4%) ተማሪዎች መወሰን አልችልም እና 5(6.7%)ተማሪዎች አልስማማምና 6(8.1) ተማሪዎች በጭራሽ አልስማማም አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በሠንጠረዥ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች ቁጥር1፣4፣7አሉታዊ ምላሾች ያሏቸው ሲሆን፤ተራ ቁጥር 5ና 10 አዎንታዊ ናቸው፡፡ምዕራፍ ሁለት በ2-3-1 ላይ ለምንባብነት የሚመረጡ ፅሑፎች አዲስና ጠቃሚ ከሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የሚያስተዋውቅ፣ የተማሪውን ዳራ ያገናዘበ፣ የመፅሐፉ ሽፋን፣ቅርፁ፣ የፅሑፉ አቀማመጥ የተማሪውን ፍላጎት ቀስቃሽ መሆን እንዳለባቸው(Nuttal1982፤Wallace1993)ያስረዳሉ፡፡

ሠንጠረዥ 12 ተማሪዎች ምንባቦቹን አንብበው መረዳት አለመረዳታቸውን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መለኪያዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጭራሽ አልስማማም | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2 | የምንባቦቹ ሃሳብ ከዚህ በፊት ከማውቃቸው ሃሳቦች ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ | 7 | 9.4 | 26 | 35.1 | 16 | 21.6 | 20 | 27 | 5 | 6.7 |
| 6 | አንድ ምንባብ ካነበብኩ በኃላ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በመለየት እንደመዘግብ መምህሬያበረታቱኛል፡፡ | 18 | 24.3 | 10 | 13.5 | 15 | 20.2 | 25 | 33.7 | 6 | 8.1 |
| 8 | ክፍል ውስጥ ምንባብ ከመነበቡ በፊት መምህሬ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ይፅፋሉ፡፡ | 22 | 29.7 | 3 | 4.0 | 12 | 16.2 | 18 | 24.3 | 19 | 25.6 |
| 9 | በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙትንምንባቦች አንብቤ ሙሉ ለሙሉ እረዳለሁ፡፡ | 9 | 12.1 | 21 | 28.3 | 15 | 20.2 | 16 | 21.6 | 13 | 17.5 |

ከላይ የሚገኘው ሠንጠረዥ 12 የሚገልፀው በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን ተማሪዎች መረዳት አለመረዳታቸውን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የምንባቦቹ ሃሳብ ከዚህ በፊት ከምታውቃቸው ሃሳቦች ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ለሚለው ጥያቄ ቁጥር 2 7(9.4%) በጣም እስማማለሁ እና 26(35.1%) እስማማለሁ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 16(21.6%)መወሰን አልችልም ሲሆን ፤20(27%) አልስማማም እና 5(6.7%) በጭራሽ አልስማማም አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡ ጥያቄ ቁጥር 6 አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በመለየት መመዝገባቸውን ለመረዳት ለቀረበው ጥያቄ 18(24.3%) በጣም እስማማለሁ 10(13.5%) እስማማለሁ አዎንታዊ ምላሽ እና15(20.2%) መወሰን አልችልም ሲሆን፤ 25(33.7%) አልስማማም 6(8.1%) በጭራሽ አልስማማም አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 8 መምህሩ ምንባብ ከመነበቡ በፊት የአዳዲስ ቃላትን ፍች መፃፋቸውን ለማረጋገጥ የቀረበ ጥያቄ ነበር፡፡ 22(29.7%) በጣም እስማማለሁ 3(4%) እስማማለሁ አዎንታዊ ምላሽ ሲያገኙ፤ 12(16.2%) መወሰን አልችልም ሲሆን ፤ 18(24.3%) አልስማማም ና 19(25.6%) በጭራሽ አልስማማም አሉታዊ ምላሽ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9 በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች አንብቤ ሙሉ ለሙሉ እረዳለሁ ለሚለው 9(12.1%) በጣም እስማማለሁ 21(28.3%) እስማማለሁ አዎንታዊ ምላሻቸውን ሲገልፁ 15(20.2%) መወሰን አልችልም ፤ 16(21.6%) አልስማማም እና 13(17.5%) በጭራሽ አልስማማም አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በሠንጠረዥ12 ላይ ከቀረቡ ጥያቄዎች ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 2 እና 9 አዎንታዊ ምላሻቸውየጎላ ነው፡፡ በተቃራኒው ጥያቄ ቁጥር 6 እና 8 ደግሞ አሉታዊ ምላሾችናቸው፡፡ ይህም መምህሩ ከንባብ በኋላ ስላነበቡት ምንባብ ፍሬ ነገር እንዲለዩና እንዲፅፉ የማያበረታቱ እና ከምንባቡ በፊት የአዳዲስ ቃላት ፍች እንደማይፅፉላቸዉ መረጃው ያሳያል፡፡ሆኖም ምዕራፍ ሁለት 2.3.2 የቃላት እውቀት መኖር አንብቦ ለመረዳት ወሳኝ በመሆኑ በንባብ ውጤታማ ለመሆን በምንባብ ውሰጥ የሚገኙ ቃላትን ተማሪው ይበልጥኑ ማወቅ እንደሚገባው (Harmer 2002፣80)ያሳስቡናል፡፡

ሠንጠረዥ 13 የምንባቦችን ርዝማኔ በተመለከተ የቀረበ ጥያቄ

| ጥያቄዎች | መለኪያዎች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን አልችልም | | አልስማማም | | በጭራሽ አልስማማም | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| እያንዳንዱ ምንባብ በአንድ ክፍለ ጊዜ ተነቦ የሚያልቅ ዝርማኔ አለው፡፡ | 17 | 22.97 | 33 | 44.59 | 9 | 12.16 | 8 | 10.81 | 7 | 9.45 |

ሠንጠረዥ 13 የሚያሳየው በመማሪያ መፅሐፋ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች በአንድ ክፍለ ጊዜ ተነቦ የሚያልቅ ርዝማኔ እንዳላቸው ለማረጋገጥ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ 17(22.9%) በጣም እስማማለሁ፤33(44.5%) እስማማለሁ አዎንታዊ ምላሾች ናቸው፡፡ 9(12.1%) መወሰን አልችልም ሲሆን፤ 8(10.8%) አልስማማም እና 7(9.4%) በጭራሽ አልስማማም የሚል አሉታዊ ምላሾች ናቸው፡፡ ከተገኘው መረጃ በመነሳት እያንዳንዱ ምንባብ በአንድ ክፍለጊዜ ተነቦ የሚያልቅ ዝርማኔ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ በምዕራፍ ሁለት 2-3-5 ላይ የምንባብ ርዝመት በተማሪዎች የንባብ ክሂል ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል፡፡ ተማሪው በንባብነት የቀረበለትን በተሰጠው ሰዓት አንብቦ ካልጨረሰ የመሰላቸት እንዲሁም እራሱን እንደ ደካማ ስለሚቆጥር በትምህርቱ ውጤታማ አይሆንም (Day and park 2005፣20)፡፡

በክፍል ሶስት የቀረበው ጥያቄ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን በተመለከተ ተጨማሪ አስተያየት ካለ በክፍት ቦታው ላይ ያስፍሩ የሚል ነበር፤ለዚህም አስተያየት ከፃፉት ይልቅ አስተያየት ያልፃፉ ተማሪዎች ቁጥር ይበዛል፡፡ አስተያየት የፃፉ ተማሪዎችም ቢሆኑ ከተጠየቁት ጥያቄ ወጣ ያለ አስተያየት የፃፉ አሉ፡፡አስተያየት የፃፉ ተማሪዎች በአብዛኛው ያንፀባረቁት ሀሳብ፤

- የመፅሐፉ መጠን አነስተኛ በመሆኑ ለአያያዝ አመቺ ነው፣
- በመፅሐፉ የተሻለ ሊያስተምሩ የሚችሉ እና አሰደሳችየሆኑ ይዘቶችን ቢያካተት፣
- በሳምንት የክፍለ ጊዜ ብዛት ቢጨመር ፣
- ከመፅሐፉ በስተጀርባ የሚገኑ ፊሊጦች በዝተው ቢቀርቡ፣
- የምንባቦቹ ርዕሶችና ይዘቶቹ የበለጠ ተጣጥመው ቢቀርቡ፣

የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ይዘታቸው ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲኖራቸው ተነሳሽነት የሚፈጥር ፣የምንባቦቹ ርዕሶችና ይዘቶቹ የበለጠ ተጣጥመው መቅረብ እንዳለባቸውእና የክፍለ ጊዜ ስርጭቱ መጨመር እንዳለበት ጥናቱ የመለክታል፡፡

## 4.3 በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለፀው ጥናቱን ለማካሄድ ከአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችን በተመለከተ መረጃዎችን በቃለመጠይቅ ከመምህራን ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ጥናቱ በተካሔደባቸው ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥየአማርኛ ቋንቋንለሚያስተምሩ መምህራን ቀርቦ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ቃለ መጠይቁ የተደረገው መምህራኑ በሚያስተምሩባቸው ትምህርት ቤቶች መላሾቹ በሰጡት ቀን እና የሰዓት ቀጠሮ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ቃለመጠይቁ አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤትከመምህርት አንድ ጋርበ9/9/08ዓ.ም.ከቀኑ 8፡00 -8፡45 ፣ከመምህርት ሁለት ጋር ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10/9/08 ዓ.ም.ጠዋት 3፡00-40፡00 ፣እንዲሁም ከመምህር ሶስት ጋር አዳሬ ሚሌኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ12/9/08ዓ.ም. ከረፋዱ 4፡05-4፡50ባሉት ጊዜያት ተካሒዷል፡፡ ቃለ መጠይቁ ሰባት ጥያቄዎችን እና አንድ ተጨማሪ አስተያየት የሚሰጡበት ክፍት ቦታ የያዘ ነው፡፡ ቃለመጠይቁ የተደረገላቸው መምህራን አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች በድምሩ ሦስት ሲሆኑ ፣ለመምህራኑ በመጀመሪያ የቀረበው ጥያቄ የትምህርትደረጃ፣የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት እና የአገለገሉት ዘመንንየሚመለከት ነው፡፡ ከእነሱ በተገኘው መረጃ መሠረት ከ40-50 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ

የሚገኙ ሲሆኑ በማስተማር ሙያቸው ከ10 ዓመት በላይ ስለሆኑ የዳበረ ልምድ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ በመቀጠል ሦስቱም መምህራን የሰጡትን ምላሽ ሀሳባቸውን በማጠቃለል በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

1 ለመምህራኑ የቀረበው የመጀመሪያው ጥያቄ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ የምንባቡ ቃሎች ለተማሪዎቹ ተስማሚ ስለመሆናቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሦስቱም መምህራን ተቀራራቢና ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ለምሳሌ መምህርት አንድ፣

በተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አስር የተለያዩ ምንባቦችን እናገኛለን፡፡ የምንባቡ ቃሎች ለተማሪዎች ተስማሚ ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎቻችንን በሁለት ክፍሎ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡ስለሆነም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑና አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን እናገኛለን፡፡ ከዚህ አንፃር አማርኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ምንባቦቹ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃሎች ይከብዳቸዋል፡፡ ሆኖም ሌሎች የምንባቡ ቃሎች ይመጥናቸዋል፡፡ ይሁንእንጂ በአማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎች ስናጤንአዳዲስ ቃሎችን ብቻ ሳይሆን የሚዘወተሩ ቃላትን መረዳት የሚከብዳቸው አሉ፡፡በአጠቃላይከመፅሐፉ መጨረሻ ገፅ ላይ መድበለ ቃላት መዘጋጀቱ ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ያቃልለዋል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡(መምህርት አንድ ፣9/9/08፣8፡45)

2 ምንባቦቹ የተማሪዎቹን ዳራ ያገናዘቡ ናቸው?

መምህራኑ ሁለት አይነት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የመጀመሪያዋ መምህርት ይህንን የምመልሰው በተራ ቁጥር አንድ ላይ ያነሳሁትን ሃሳብ በመድገም ነው፡፡ በትምህርት ቤታችን ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች (50%) የሚሆኑ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ናቸው፡፡

በመፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንዳንድ ምንባቦች ደግሞ ከሚያውቁት ማህበረሰብ ባህል ወጣ ያለ በመሆኑ የተማሪዎቹን ዳራ ሙሉ በሙሉ ያገናዘበ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ሌሎች ሁለቱ መምህራን የሰጡት ምላሽ የመጀመሪያውን ሃሳብ የሚቃረን ነው፡፡ ይኸውም በምንባብነት የቀረቡት ክልሉን የሚገልፁ ይገኙበታል፡፡ የእኛም ተማሪዎች በማንበብ የሌሎችን ባህል ማወቅ እና እነሱ ከሚያውቁት ባህል ጋር ማወዳደር የሚችሉት በማንበብ ነው፡፡ ስለዚህ ሚዛናዊ ናቸው፡፡

3. የምንባቦቹን ሃሳብ በክፍል ደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች አንብበው ይረዳሉ?

ይህን ጥያቄ በተመለከተ የመጀመሪያው መምህርከዚህ በፊት ለነበሩ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተነሱ ሃሳቦች በዚህ ጥያቄ ምላሽ ላይ ለማንሳት እገደዳለሁ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ሁለት አይነት ተማሪዎች ናቸው፡፡ አማርኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ያነባሉ ሲጠየቁ ባነበቡት መሠረት ይመልሳሉ፡፡ ይህ ደግሞ መረዳታቸውን ያሳያል፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ መምህራን የመጀመሪያውን ሃሳብ እንደሚጋሩ በመግለፅ በተጨማሪ የገለፁት ሃሳብ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች በንባብ ወቅት ተሳትፎ የሌላቸው እና ከርዕሱ ጀምሮ መረዳት እንደሚከብዳቸው ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ሆኖ ተነሳሽነት ያላቸው አንብበው የሚረዱ የተሻለ የሚሰሩ ተማሪዎች እንዳሉ መረሳት እንደሌለበት ጠቁመዋል፡፡

4. የመፅሐፉ መጠን፣ ሽፋን፣ ህትመቱ የምንባቦቹ አቀማመጥ የተማሪውን ፍላጎትለንባብ ቀስቃሽ ናቸው?

ከመምህራኑ የተሰጠው ምላሽ የመፅሐፉ መጠን ለአያያዝ አመቺ እና ከተማሪዎች ቦርሳ እና ከደብተራቸው ጋር የሚመጣጠን ነው፡፡ ሽፋኑ በሚመለከት የሀገራችንን ባንዲራ እና ከቋንቋ ትምህርት አላማ አኳያ የክሂል ዘርፎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ በትክክል የሚገልፅ፣ ስዕሉን በማየት እነዚህን ነገሮች እንዲመራመሩ ዕድል የሰጠ በመሆኑ ሳቢነትና ማራኪነቱ ትምህርታዊና ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪ የምንባቦቹ ህትመትና አቀማመጥ ግልፅ ለማንበብ ምንም የማያስቸግር ከርዕሶቹ ጀምሮ ማራኪነት አላቸው፡፡

5. በመፅሐፉማውጫ ላይ የምንባቡ ርዕሶች በግልፅ ተቀምጠዋል?

መምህራኑለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም ከማውጫው ላይ ርዕሶቹ በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ አብይ ርዕሱና ንዑስ ርዕሱ በግልፅ መቀመጡ ሳቢነት ኖሮት ተማሪዎች ለንባብ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ይጋብዛል፡፡

6. በየምዕራፉየምንባቦቹ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች ለተማሪው ፍላጎት ተስማሚናቸው?

ከመምህራኑ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች አሰልቺነት የማይታይባቸው ግልፅ ሆነው የቀረቡ ናቸው ፡፡ አንድ ምንባብ ጨርሰን ወደ ሌላው

ርዕስ ስንሸጋገር የተማሪዎች ፍላጎት እንዳጤንኩት ከሆነምንም አይነት ተፅኖ አልፈጠረባቸውም፡፡ ስለዚህ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶቹ ለተማሪው ፍላጎት ተስማሚ ናቸው፡፡

7. የምንባቦቹ ይዘቶች ወቅታዊ አዳዲስና ጠቃሚ ርዕስ ጉዳዮችን ያገናዘቡ ናቸው?

ለዚህ ጥያቄመምህራኑ የሰጡት ምላሽ ከተወሰኑ ይዘቶች በስተቀር ተማሪዎችን ከአዳዲስ ፈጠራዎች ፣ግኝቶች ተማሪው እንዲያነበው የሚያጓጉ ይዘቶች ጎልተው አይታዩም ፡፡ ሰለዚህ የምንባብ ይዘት ሲመረጥ የተማሪውን ዕድሜ የሚመጥን እንዲሆን ሊታሰብበት ይገባል፡፡

በመጨረሻም ከሶስቱም መምህራን ምንባቦቹን በተመለከተ አስተያየት ተጠይቀው ነበር፡፡ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ ፤በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ከተማሪው ጋር ለመስራት ቀደም ብለው የተጠቀሱ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩምየተመደበው ክፍለ ጊዜ ዝቅተኛ መሆንበተለይም አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸውየሆኑ ተማሪዎች በቂ የልምምድ ጊዜ አይኖራቸውም ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተማሪዎች ከክፍለጊዜው ውጭ በቋንቋው ለመግባባት ናለማንበብ ያላቸው ጥረት ጎልቶ አይታይም ፡፡ ይህ አስተያየት ደግሞ ተማሪዎች በነፃ አስተያየት መስጫ ቦታ ላይ ካሠፈሩት ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2004 ዓ.ም በታተመው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃዉ ያላቸውን ተነባቢነት መፈተሽ እንደሆነ በጥናቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ተገልጿል፡፡በዚህ ዋና ዓላማ/ሥር በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃዉ ያላቸውን ተነባቢነት መፈተሽ፣ምንባቦቹ ለተማሪዎች የምንባብ ፍላጎት ተነሳሽነት ያላቸው አስተዋፅኦ መመርመርና ተማሪዎቹ ምንባቦችን አንብበው በበቂ ሁኔታ መረዳት አለመረዳታቸውን መለየት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች ተካተዋል፡፡እነዚህን አላማዎች ለማሳካት የጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጭ የሆነው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ናቸው፡፡

ጥናቱ የተካሔደባችው ትምህርት ቤቶች በተራ ዕጣ ናሙና አመራረጥ ስልት ተወስደዋል፡፡በየትምርት ቤቱ የሚገኙ የምድቦች ብዛት ከታወቀ በኃላ ከየትምህርትቤቱ በተራ ዕጣ ናሙና ስልት ሶስት፤ ሶስት በድምሩ 9(ዘጠኝ)ምድቦች ተመርጠዋል፡፡በረድፋዊ ንሞና ዘዴ የተመረጡተማሪዎች ከየምድቡ አንድ አምስተኛለመውሰድ አምስት፤ አምስት ተማሪዎችን በመዝለል በአጠቃላይ 90(ዘጠና) ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

የመምህራንን ናሙና አመራረጥ በተመለከተ በሁለቱ ትምህርትቤቶች የሚገኙ መምህራን ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ጥናቱ ከተካሄደባቸው ሁለቱ ትምርትቤቶች ያሉት በሙሉ ሲወሰዱ በአዲስከተማ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ግን ተራ ዕጣ ናሙና ስልትን በመጠቀም አንድ መምህር በድምሩ 3(ሶስት) መምህራን የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በመሆን ተግባራዊ የተደረገው በሰነድ ፍተሻ የመፅሐፉን ምንባቦች በመውሰድ የስሌት ውጤት መግለፅና፣ ለተማሪዎች የቀረበ የግንዛቤ ሙከራ  በዋናነት ሲጠቀሱ፣ የፅሑፍ መጠይቅና በተጠኚ ትምህርት ቤቶች

የአማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ በአጋዥነት የቀረቡ ናቸው፡፡

ከመማሪያ መፅሐፉ መጀመሪያ ፣መካከልና መጨረሻ ላይ ምንባቦችን በመውሰድእና የFlesch ቀመርን ተግባራዊ በማድረግ የናሙና አንድ የንባብ ቅለትነጥብየስሌት ውጤት -26፣የናሙና ሁለት የንባብ ቅለት ነጥብ የስሌት ውጤት -9እና የናሙና ሦስት የንባብ ቅለት ነጥብ የስሌት ውጤት -22 ሲሆን ምንባቦቹ ተነባቢነት እንደሌላቸው የሚገልፁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ከዚህ ውጤት አንፃር ሶስቱም ናሙና ምንባቦች በተናጠል የሚገመቱት ከሚገኙበት ክፍል ደረጃ በላይ እንዲሁም ፣የሦስቱም ናሙና ምንባቦች አማካይ ውጤት የሚያሳየው -19 በመሆኑ የመፅሐፉ ምንባቦች የሚገመቱት ከሌጅን ላጠናቀቁ መሆን እንደሚገባው መረጃው ይጠቁማል፡፡በምዕራፍ ሁለት የምሁራኑ ሀሳብ የFlesch ቀላል የንባብ ነጥብ አሰጣጥ እንደሚያሳየው0-29 በጣም ከባድ እና ኮሌጅን ላጠናቀቁ መሆን እንደሚገባው ያስረዳል፡፡ከላይ የተገለጹት የእያንዳንዱ ናሙና እና የሦስቱም ናሙና አማካይየስሌት ውጤት የሆኑት ቁጥሮች ማለትም -26፣-9 ፣-22ና -19 ከዜሮ በታች መሆናቸው የምንባቡን ክብደት ደረጃ ያስረዳሉ፡፡

የምንባቦቹ ተነባቢነት በFryግራፍም ተለክቷል፡፡ እያንዳንዱን ናሙና ምንባብ ውጤት በመውሰድ በFry ግራፍ ላይ ሲሰፍር የእያንዳንዱ ምንባብም ሆነ የሶስቱ ናሙና ምንባቦች ስሌት ውጤት እንደሚያመለክተው ምንባቦቹ በተመደቡበት ክፍል ደረጃ ተነባቢነት የሌላቸውና ከ19ኛ ክፍል በላይ እንደሆኑ የFry ግራፍ ያስረዳል፡፡ በአጠቃላይ የFlesch ቀመርና የFry ግራፍ ውጤት ምንባቦቹ ተነባቢነት እንደሌላቸው ያረጋግጣል፡፡ስለዚህ በምዕራፍ አንድ ላይ ለጥናቱ በመሪ ጥያቄነት ከተነሱት የመጀመሪያው ጥያቄ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ተነባቢነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በቀመር ስሌቱ መሠረት ምንባቦቹ ተነባቢነት እንደሌላቸው ተረጋግጧል፡፡

የግንዛቤ ሙከራዎቹ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ በተመረጡት ትምህርትቤቶችየሚማሩ ተጠኚ ተማሪዎች ተፈትነዋል፡፡ ፈተናዎቹ በአራሚ 1፣2 እና 3 ታርመዉውጤቶቹ ከ100 ሲሰሉ ከፈተናዎቹ የተገኙ ውጤቶች ተቀራራቢ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በአራሚዎቹ መካከል ስምምነት መኖሩን በመደበኛ ልይይት (ANOVA )

ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ውጤት 0.05 በላይ መሆኑ በአራሚዎች መካከል ስምምነት መኖሩን ያመለክታል፡፡አባሪ 9ኝንይመልከቱ፡፡እያንዳንዱ የግንዛቤ ሙከራ ውጤት ሲጤን ሙከራ አንድ ከሙከራ ሁለት የተሻለ ነው፡፡ የሙከራ ሁለት ውጤት ደግሞ ከሙከራ ሦስት የተሻለ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ምንባቦቹ እየከበዱ መሄዳቸውን ነው፡፡ ለምሳሌ ሙከራ አንድ ላይ8(12.6%) ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚያነቡ፤28(44.4%)ተማሪዎች ለማንበብ የመምህር ድጋፍየሚፈልጉ እና 27(42.8%) ተማሪዎች ደግሞበጭንቀት በሚያነቡበት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡በአንፃሩ ግን ሙከራ ሁለት 3(4.76%)ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚያነቡ፤30(47.6%) ተማሪዎች የመምህር ድጋፍ የሚፈልጉ እና 30(47.6%) ተማሪዎች በጭንቀት የማንበብ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ፤ በሙከራ ሶስት ራሳቸውን ችለው የሚያነቡ ተማሪዎች የሉም፡፡ 26(41.2%)ተማሪዎች በመምህር ድጋፍ የሚያነቡ እና 37(58.7%)በጭንቀት በሚያነቡበት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

በመጨረሻም የሦስቱ ፈተናዎች ጥቅል አማካይ ውጤት 36(57.1%) ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ የሚያነቡ ስለሆነ ለተሻለ ውጤት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ያረጋግጣል፡፡ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘውም ምላሽ “ምንባቦችን አንብቤ ሙሉ ለሙሉ እረዳለሁ” የሚል ቢሆንም ከፈተናዎቹ (ከሙከራዎቹ)ውጤት ጋር ተጣጣሚነት የለውም፡፡ በተራ ቁጥር ሦስት ለተነሳው ለጥናቱ መሪ ጥያቄ ምላሹ በበቂ ሁኔታ ይረዱታል ሳይሆንከስፈረው መረጃ በመነሳት መካከለኛ(የመምህር ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው) ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

ለተጠኚ ተማሪዎች የተሰራጨ የፅሑፍ መጠይቅ ተማሪዎች ዘንድ ከመድረሱ በፊት በክሮኾባን አልፋ ሲረጋገጥ ውጤቱ 0.87 መሆኑ የመጠይቆቹን አስተማማኝነት ያረጋግጣል፡፡ አባሪ 8 ይመልከቱ፡፡ በመሆኑም የመጠይቁ ምላሽ እንደሚያሳየው ተማሪዎቹበምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን መረዳት ይከብዳቸዋል፡፡ በሌላ አገላለፅ ቃላቱን ካልተረዱ ምንባቦቹ ተማሪዎች ለሚገኙበት ክፍል ደረጃ ተነባቢነት አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ አስመልክተው ምዕራፍ ሁለት 2.3.2 አንባቢው በፅሑፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ከግማሽ በላይ የማያውቃቸው ከሆነ አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘትና ለመረዳት ይቸገራል፡፡ ውጤታማ ለመሆን ይበልጡን ቃላት የሚያውቃቸው

መሆን አለበት(Harmer 2001፣80)። ከዚህ ሀሳብ በመነሳትና ከመጠይቁ የተገኘውን ምላሽ መሠረት በማድረግ ለተማሪዎቹ የምንባቡ ቃሎች ይከብዳቸዋል።

በተጨማሪ ምንባቦቹ ከወቅታዊ ፤አዲስና ጠቃሚ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር እንዲተዋወቅ አያደርጉም ፤ ይህም ለመምህራኑ ለቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ከተማሪዎች ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ነው።ስለዚህ አዲስ ጠቃሚና አስተማሪ የሆኑ የተማሪዎችንዕድሜ የሚመጥኑ ጉዳዮችን ለንባብ ማቅረብ፤እንዲሁም ዳራቸውን ማገናዘብናይዘቱ ለተማሪዎች ፍላጎት ተስማሚ መሆን አማራጭ የሌለው ነው።

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በማወያየት ስለ ምንባቡ ፍንጭ አግኝተው እንዲያነቡ ማበረታታትና ፍላጎት ማሳደር መምህራኑ ይጠበቅባቸዋል።እንዲሁም ከንባብ በኃላ ፍሬ ሃሳብ በመለየት እንዲመዘግቡ አለማድረግ ጥረት አድርገው እንዳያነቡና ቸልተኛ እንዲሆኑ ይጋብዛል።በአጠቃላይ በሁለተኛ ደረጃ ለተነሳው ለጥናቱ መሪ ጥያቄ የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ፍላጎት ተስማሚ መሆን /አለመሆናቸው ማረጋገጥ ነበር።ስለዚህ ከላይ የተነሱ ሀሳቦች ማለት የምንባቦቹ ቃላት መክበድ ፣ወቅታዊ ና አዲስ ይዘቶችን አለማካተት የምንባቦች የይዘት ተስማሚነት ማጣት ምክንያት ናቸው።

ምንባቦች ለአንድ ክፍለጊዜ የሚመጥን ርዝማኔ አላቸው፤የመፅሐፉ ሽፋን፣ ቅርፅ፣ ህትመቱ ለንባብ ፍላጎት የቀስቃሽነት ሚና አላቸው። ከቃለ መጠይቅና ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች ሲሆኑ ፤ከመፅሐፉ ጠንካራ ጎኖች የሚጠቀሱ ናቸው።

## 5.2 አስተያየት

- በቀመር የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የምንባቦቹ ተነባቢነት ከሚገኙበት ክፍል ደረጃ በላይ እንደሆነ በትንተናው ክፍል ተረጋግጧል፡፡ በግንዛቤ ሙከራ ውጤትም የተማሪዎች መረዳት ችሎታ መካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝና ለተሻለ ውጤት የመምህር ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው መረጃው ያሳያል፡፡ ከፅሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ የምንባቡ ቃሎች ይከብዳሉ የሚል ነው፡፡ እነዚህ የተደጋገፉ ምላሾችን በመያዝ ምንባቦች በሚዘጋጁበት ጊዜ ለዚያ ክፍል ደረጃ ተነባቢነታቸውንለመፈተሽ የቋንቋው (የክፍለ ትምህርቱ) ባለሙያዎችእና ሌሎችጥናት አድርገው በመለኪያነት የሚያገለግሉ መመዘኛዎች አገልግሎት ላይ ቢውሉ፤
- ተማሪዎች ስለምንባቡ ፍንጭ አግኝተው የንባብ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ ውይይት የማድረግ ልምድ እንዲያጎለብቱ ጥረት ቢያደርጉ፤
- ከተማሪዎች ፅሑፍ መጠይቅና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽእንደሚያመለክተው ተማሪዎች የምንባቦቹ ቃሎችይከብዷቸዋል፡፡ ስለዚህ ምንባቦች ከመነበባቸው በፊት መምህራን ለአዳዲስ ቃላት ፍች ቢፅፉላቸው፤
- የዕለቱን ምንባብ ማንበባቸውንና መረዳታቸውን ለማወቅ መምህራን ከንባብ በኃላ ተማሪዎቹስላነበቡት ነገር መልዕክቱን እንዲፅፉ መምህራን ቢያበረታቷቸው፤በቸልተኝነት እንዳያልፉና በአትክሮት እንዲያነቡ ይረዳል፡፡
- የመፅሐፍ አዘጋጆች ለምንባብነት የሚቀርቡ ፅሑፎች ወቅታዊ አዲስና ጠቃሚ ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ የተዘጋጁ ፤በተቻለ መጠን በአካባቢው ማህበራዊ ህይወት ላይ ያተኮሩና ባቀራረባቸው ሳቢና ማራኪ እንዲሆኑ ጥረት ቢያደርጉ፤
- በክፍል ደረጃው የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚያደርጉት እገዛ ልዩ ትኩረት ቢሰጠው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


መሰሉ መንግስቱ፡፡(1994ዓ.ም.)፡፡የማስተማር ስነዘዴ፡፡ዲላ መምህራንጤና ሳይንስ ኮሌጅ፡፡(ያልታተመ)

ስዩም ከበደ፡፡(1994ዓ.ም.)፡፡አማርኛን የማስተማር ሥነዘዴ ፡፡; ሀዋሳ መምህራን ትምህርትኮሌጅ፣(ያልታተመ)

በድሉዋቅጅራ፡፡(1996ዓ.ም)፡፡*በሥነፅሑፍቋንቋንማስተማር*፡አዲስአበባ፣ንግድማተሚያ ድርጅት

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡(2004 ዓ .ም)፡፡*አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ 10ኛ ክፍል*።(1ኛእትም) አዲስአበባየኤል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅትናኩራዝኢንተርናሽናልአሳታሚኃ/የተ/የግ/ማህበር

ካሴ አለሙ፡፡ (1998 ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ታሪካዊ ዳራ 1940-1966 ዓ.ም.አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ወንድወሰን፡፡ (2004 ዓ.ም)፡፡ለአንደኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል /5-8ኛ/ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያበተማሪ ተኮር ሥነዘዴ ለማስተማር ያላቸው የአዘገጃጀት መቹነት;፡፡ሀዋሳ መምህራን ኮሌጅየጥናትና ህትመት ማሰተባበሪያ ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ፡፡(ያልታተመ)

ያለው እንዳወቅ ሙሉ፡፡ (2004 ዓ.ም)፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡* (3ኛእትም) አዲስ አበባ፣ ባህዳር ዳር ዩኒቨርስቲ፡፡

ጌታቸው አዱኛ፡፡ (1986 ዓ.ም)፡፡ ለ10ኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ፡፡; አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች፣ለሥርዓተ ትምህርቶች፣ ለመማሪያ መፃህፍትና ስለሥነ ፅሑፍ ሚናበቋንቋ ትምህርት (1994-1982 ዓ.ም.)፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ ለቋንቋዎች ጥናትተቋም ዘጠነኛ ሴሚናር የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

ፍቃዱ ማሙዬ።(1995)።በኦሮሚያ ክልል ለሰባተኛናለስምንተኛ ክፍል የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች አዘገጃጀት ግምገማ ።ዲላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለድግሪ ማሟያ የቀረበ ።(ያልታተመ)

Alderson, J.c.(2001). *Assessing Reading*. Cambridge: Cambridge University press.

Arthur Hughes (1992).*Testing for language Teachers( 4th ed).*Cambridge:Cambridge University press.

Berhe kahisay (1989) "A study of the readability level of grade ten text books and the comprehension abilityof the students using them.." unpublished M.A theses, AddisAbaba university.

Clark,H.L.andStarr.s.(1986).*secondaryandmiddle school teaching methods*.5thed.NewYor MAGMILLUAN

Collie.J.and S.Slater (1987 ) *Literature in the language Classroom*. Cambridge:CUP.

Day,R.R.and park,J.(2005). Developing reading comprehension Questions. ReadinginforeignlanguageJournal.Vol.17,No.1.Available:http://nflrc.hawaii.edu /rfl(Accessed on October 8,2015)

DuBay. WH.(2004).The principle of readability. Journal of educational research Vol.2.No . 7,PP. 1-70 from http;// WWW nald.calf full text /readab/ readab.(Accessed on October 17,2015)

Grabe,W. (2009) *Reading in a second language moving from theory to practice*. Cambridge: Cambridge

Harmer.J.(2002). *The practice of English language teaching (3rded). Harlow,* ESSex: langman.

Hsuech-chao.M.and Nation.P.(2000).Unknown vocabulary Density and Reading comprehension.Reading in aforeignlanguage Journal. VOl.13.No.1Available:http://of lre.hawaii-edu/rfl(Accessed on October 2,2015)

Larson L.M.(1984). *Aguide to cross language equivalence.* London:America university press. InC

Mehari yimulaw (2004)"Readability level assessment of Tigiringa textbook for grade four students."Unpublished M.A theses, AddisAbaba University.

NasserM.F.(2014).TheoryandpracticeinlanguageStudies.vol.4.NO.10.pp.2042-2050.october 2014 ACADEMY PUPLISHER mnufacturedin Finland. doi:10.4304 (Accessed on December 3,2015)

Nuttal,C(1982). *Teaching Reading skills in Aforeign Language* .Londan: Heinemann.university press

Vacca,T.R.and vacca,L.J(1998).*Content Area Reading Literacy and Learning Across the Curriculum 6th ed.* Newyork:longman,Inc

Wallace,C.(1993).*Reading.*Newyork:Oxford

Williams,E.(1984). *Reading in the language classroom.* London: macmillian publishers. Ltd.,

Zamanian.M.(2012). Theory and practice language studies. Vol.2.No.7,pp.43-53 2012 dio:10 4304/tpls.2.1. 43-53 ACADEMY PUBLISHER manufactured in finland. (Accessed on December 3,2015)

# አባሪዎች

## ሙዳዩ ቃሎች

ተነባቢነት ---------- ተነባቢነት ለተማሪዎች በሚመጥን ቋንቋ ለደረጃ ተስማሚ ሆነ የቀረበምንባብ/በቀላሉየሚነበብፅሑፍ

የቀመር ውጤት----- ምንባቦችናቀመሮችን በመጠቀም በስሌት የተነባቢነትን ደረጃ የሚያሳይ ውጤት

የንባብ ቅለት ነጥብ-------- በቀመር ስሌት የተገኘው ውጤት ምንባቡ ለየትኛው ክፍልደረጃ እንደተገመተ የሚገልፅ

የግንዛቤ ሙከራ-------- ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ ምን ያህል እንደተረዱት፣እንዳስተዋሉት ለመገምገም የሚሰጥ ፈተና

## አባሪ 1

### Edward Fry(1977)graphy




Source: Zamanian 2012:46

አባሪ 2

## የናሙና ምንባቦች ቀለም ብዛት

## ናሙና አንድ ቀለም

| ተ.ቁ | ቃሎችና ሀረጎች | በአንድ ቃል ውስጥ የቀለም ብዛት+ |
|---|---|---|
| 1. | ቋንቋ | 4 |
| 2. | አንደበታዊ | 5 |
| 3. | ስርዓታዊ | 4 |
| 4. | የሆነ | 3 |
| 5. | የሰው | 2 |
| 6. | ልጅ | 1 |
| 7. | መግባቢያ | 4 |
| 8. | መሣሪያ | 4 |
| 9. | ነው | 1 |
| 10. | ይህን | 2 |
| 11. | መሣሪያ | 4 |
| 12 | መቸእና | 3 |
